# ትግላችን ዜና


ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

Prepared by the Ethiopian Students Union
in Europe

P.O.Box 3198, 10364 Stockholm 3 SWEDEN


## በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ፲፯ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርና የፖለቲካ ውሳኔ


VOL. 5 No. 1
September 1977

ቁጥር ፩
ነሐሴ ፲፱፻፷፱



ጓድ አብዱላሂ ዩሱፍ

የቀድሞ የኢሲተማ ኘሬዜዳንት

“እንተ ለተሰዋህለት አብዮት እኛም እስከደማቸን ጠብታ እንታገላለን”

ትግላቸን ዜና

Stockholm August 20, 1977

## ስለ ጓድ አብዱላሂ የሱፍ ሞት
## በኢ.ተ.ማ የወጣ መግለጫ፤

አብዮት በሚካሄድበት ወቅት አያሌ ነገሮች ተሰበጣጥረው ይገኛሉ:: የዐረ አብዮት ወገን አብዮቱን ለመግታት ዘወትር ይፍጨረጨራል:: አብዮታውያን ደግሞ አብዮቱን ወደፊት እንዲራመድና ተራምዶም ከግቡ ይደርስ ዘንድ ይታገላሉ:: በነዚህ ሁለት ኃይሎች መካከል ከፍተኛ ትንቅንቅ ይካሄዳል:: ትግሉ ከእለት ወደእለት እየከረረ ሲሄድ የለየለት አድሃሪ ፋሺስት ብቻ ይሆን የተረማጅ ለምድ የለበሰውም የጥቅም ጉዳይ በሰሆነ የግድ አውነተኛ ፊቱን እንዲያሳይ ይገደዳል:: አብዮቱ ከሠመረ ጥቅሙን ያጣልና:: ስለዚህም አብዮቱ ወደፊት ከመገፋቱ በፊት ለመግታት በአብዮታውያን ላይ አምርሮ ይነሳል:: አይገቡ ገብቶ የአብዮታውያንን ዱመጥማጥ ለማጥፋት በደነበ የተቀነባበረ ግድያ ይፈጽማል:: የጓድ አብዱላሂ አህመድ ሞትና ከዚህ በፊት በአብዮቱ ሜዳ ላይ ህይወታቸውን ያጡት ቀን ተረማጆች ሁኔታ ከዚህ የመነጨ ነበር::

ሆኖም የገዳይ ወገን አንድ መረዳት ያለበት ነገር አለ:: ትግሉ የወሰደውን ጊዜ ወስዶ በብዙሀን ታጋዮች ደምና መስዋዕትነት ለጭቁኖች ድልን ለማጎናጸፍ ቆርጦ የተነሳ በሰሆነ ታጋዮች በጓድ አብዱላሂ ሞት ከልብ ቢያዝኑም አይደነግጡም:: እንዲያውም ጓድ አብዱላሂ እንገቡ ሲታገልለት የነበረውን መፈክር ተቀብለው እሱ ለታገለለት ዓላማ እሱ ለሞተለት እውነተኛ አብዮት እነሱም በደማቸው ወብታ ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸውን ነው :: ጓድ አብዱላሂ በኢ ተ ማ ውስጥ በልዩ ልዩ ኃላፊነት በስራ አስከያጅ ኮሚቴና በኢ.ተ.መጽሔት ቦርድ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ያሳየ ቈራጥ አብዮታዊ ነበር:: በኢ.ኢ.ተ.ማ. ከፍተኛ ጥንካሬና ጥራት እንዲኖር ለኢትዮጵያ አብዮት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ከደረጉት ጓዶች መካከል አንዱ ነበር:: ጓድ አብዱላሂ በአውሮፓ በነበረበት ወቅት የታይራኒውን ኃይለሥላሴ መንግሥት በመቃወምና ይህን ቀጥሎ ማቲፊያሳይዝ በማድረግ በልዩ ልዩ አውሮፓ ሀገሮች ከሚገኙት ተራማጅ ማህበራት ጋር በመተባበር የዚህን መንግሥት አስከፊ ድርጊቶች በየፈርጃቸው በማጋለጥ የታገለ ታላቅ አብዮታዊ ወጣት ነበር::



ጓድ አብዱላሂ የኃይለሥላሴ መንግሥት ከወደቀ በኋላ በአውሮፓ ውስጥ በተማሪ ማህበራት አካባቢ ለተደረገው ከፍተኛ የመስመር ትግል ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል:: ''ዓለም አቀፍ ፌደሬሽን'' ተብሎ የሚጠራው በአውሮፓ የሚገኘው የነአበሩ ወበን — መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት የውጭውን ንቅናቄ ከውስጥ ሆኖ በርበሮ ለማዳከም ያደረገውን ሙከራ ከንቱ ሆኖ እንዲቀር ካደረጉት ግንባር ቀደም ታጋዮች አንዱ ጓድ አብዱላሂ አህመድ ነበር:: በዚህ ወቅ ነበር ውስጥ ለፖለቲካ ጥራትና ለሁለት መስመር ትግል ያደረገውን ተጋድሎ ታሪክ ምንም ጊዜ እንደሚያስታውሰው ማህበራችን ያምንበታል::

ጓድ አብዱላሂ አውሮፓ በነበረበት ጊዜ በኢ.ኢ.ተ.ማ.ውስጥ የብሔረ—ሰቦች ጥያቄ በደንብ ተወንቶ በአባላት መካከል ትክክለኛ መግባባት ይኖረው ዘንድ አጥብቆ ታግሏል:: ራሱ ከጭቁን ብሔረ—ሰቦች አንዱ መሆኑን እያስረዳ አርገጦኛ አብዮት ወዳጆች የብሔር ጥያቄ ሁለት ሰይፍ እንዳለውና ማለትም በአንድ ወገን ጠባብ ብሔረተኝነት የሚመጣውን አደጋና በሌላ በኩል ብሔረተኝነት የብሔር ትምክተኝነት ደግሞ የዚያኑ ያህል አደገኛ በሰሆነ የሁለቱም ወገን ማርክሲስት ጠባብ ብሔርተኝነትንና ብሔርተኝነትን ሊወሩና ትክክለኛው መስመር መከተል የሚቻለው በጥናት፣ በምርምር፣ ጭምር መሆኑን በማመን በአ የኦርጅ ተማሪዎች ጥናት ክበብ (O.S S.C.E ) እንዲቋቋም የማተፊያልና የሞራል እርዳታ ከመስጠትም አልፎ ጥናት በማቅረብና በመሳተፍ የጥናት ክበቡ እነሆ ዛሬ በአ.የኢ.ተ.ማ.አባል ሆኖ አበበ እንዲሰራ ከልብ የታገለ እውነተኛ አብዮታዊ ነበር::

ከዚህ በኋላ የኢት.አብዮት በየካቲት 66 ቢፈነዳ ያለምንም ጥርጣሬና ማወላወል ለአብዮት እንደቆሙት ጓዶች በሙሉ ከአውሮፓ ወደ አብዮቱ ሜዳ ወደሀገሩ ተመለሰ:: አገር ቤትም በነበረበት ጊዜ ''የናት አገር ጥሪ'' የሚለውን መፈክር በመቀበል ለእናት አገሩ ለማገልገል በአብዮት ተሳትፎ ውስጥ በህዝብ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ጽህፈት ቤት ሥር በሐረር ጠቅላይ ገዛት በሃላፊነት ተመድቦ ለቆመለት ዓላማ በጽኑ ታግሏል:: በተለይም ከነውስ ከበርቴው ቡድን ከኢህአፖ ጋር ያደረገው ትግልና ሐረርን ያህል ሀገር በአጭር ጊዜ ከኢህአፖ ማወናበድ አጽድቶ አያሌ አገር ወዳድ ታጋዮችን አትርፏል:: ከዚህም አልፈው ለእውነተኛ አብዮት የሞው ባለ በኢህአፖ የተወናበዱትን ወደ አብዮቱ በፈር መልስ የትግል ሰው እንዳደረጋቸው በዓይናችን ሥር ያለፈ እውነት በሰሆነ ጓድ አብዱላሂን ከጭቁኖች የኢት.ህዝቦች ጉን በመቆም እንሱ ሳጡት ታጋይ ያብዮቱን መሪሪ ሀዘን እኛም እንካፈላቸዋለን:: ጓድ አብዱላሂ ለኢት.ጭቁን ህዝቦች እውነተኛ አብዮት የሚገነባው በነቃ፣ በተደራጀና በታጠቀ የህዝብ አመጽ ለመሆኑ ምንም ኢሳማን የሌለው ጓድ መሆኑን የሚያውቁ ይህንንም በአይናቸው ፊት በተግባር ሰለአረ

ጋገጠ፤ አብዮት በፊር የሚያሰሁ የሚለውን ብረክ ስለአስያዘው በጠራራ ፀሐይ በመሃል ከተማ በአድሃሪ ጥይት ተመቶ ወድቋል:: ማህበራችን በጓዱ አብዱላሂ ሞት ከልብ ያዝናል::

ስለዚህም ከኦገስት 8—14 በስዊዘርላንድ የተደረገው በአ.ኢ.ተ.ማ. የ17ኛው ጉባኤችን በጠቅላላው ለጭቁን ህዝቦች ነፃነት ሲታገሉ የወደቁትን አያስታወሰ ጉባኤው ጓድ ፍቅሬ መርአድ የቀድሞ የታጠቀ መጽሔት አዘጋጅ ጓድ አብዱላሂ አህመድ የቀድሞ የአ.ኢ.ተ.ማ.ፕሬዚዳንት ለእውነተኛ ነፃነት ሲታገሉ የወደቁትን እርማ አንስቶ ትግሉን ለመቀጠል ቃል ኪዳን የገባበት ጉባኤ እንደሆነ በአብዮታዊ ስሜት እንገልጻለን::

ማህበራችን ''አብዮታውያን ይሞታሉ እንጂ አብዮት አይሞትም'' የሚለውን መርህ በመከተል ጓድ አብዱላሂ ይዞት ሲታገል የወደቀውን መፈክሮች እኛ አንስተን ትግላችንን በቆራጥነት ወደፊት እንገፋለን:: እንተ ለተበዋሃለት አብዮት እኛም እስከደማችን ጠብታ እንታገላለን:: ዘት ውልድ ትውልድ ይሸጋገራል እንጂ እንተ የሞትክለት አብዮት አይታጠፍም:: ቀኑህ የአብዮታውያንን ለአብዮት ያላቸውን የመጨረሻ መስዋእትነት በሰሚያስመሰከር አርአያውን አብዮታውያን በሙሉ ይከተሉታል::

ገዓይና ተበባሪዎች ለአብዮታዊ ፍርድ ይቀረቡ !
ታጋይ ሰሞት ትግል አንዓይሞት የቢሮክራሲውን አሻጥር እንቷቷም !
አብዮታችንን ወደአጥቂነት እናሸጋግር !
ዲሞክራሲ ለጭቁኖች አሁን !
የነፃ፤የተደራጀና የታጠቀ የህዝቦች ትግል ያሸንፋል::

ስለ አኢተማ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

THE ETHIOPIAN STUDENTS' UNION IN EUROPE



## በአኢተማ 17ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት

በአውሮፖ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ በሉዛን /ስዊስ/ ከተማ ከ8/8/77 እስከ 14/8/77 አብዮታዊ የትግል መንፈስ በተመላበት አኳኋን ተካሄዷል::

ይህ ጉባዔ የተደረገው የኢትዮጵያ ህዝቦች ለነፃነታቸውና ለትግላቸው የሚያደርጉት ትግል እየተፋፋመ በዙም ድሎች እየተጎናፀፉ በመጡበትና በአንፃሩም የአብዮቱ ጠላቶች ኃይላቸውን ከውስጥና ከውጭ አጣምረው የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ በሚፍጨረጨሩበት ወቅት ነበር::

የኢትዮጵያ አብዮት ከፈነዳበት ከየካቲት 66 ዓ.ም. ጀምሮ የአብዮቱ ወዳጆችና ጠላቶች መስካቸውን በግልጽ እያሳመረ መጥተው እነሆ ባሁኑ ዓመት የጠላት ወገኖች ኢምፔሪያሊዝም፤ ፊውዳሊዝምና ቢሮክራቲያዊ ካፒታሊዝም ሰፊውን ሕዝብ በመፈንቀለ መንግሥት በኢኮኖሚ አሻጥርና እንዲሁም ከአድሃሪ የጎረቤት አገሮች መንግሥታት ጋር በመተባበር በአብዮቱ ላይ ግልጽ ጦርነት የከፈቱበትና የተፈታተኑበት ወቅት ነበር::

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በማያወላውል ሁኔታ የቆመ መጠበር መሆኑን ደግሞ ደጋግሞም ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በትግሉ ሜዳ በየጊዜው የሚሰውትን የጓደኞችን እርማ በማንሳት ለሚታገለለት "ለነፃ፤ ለተደራጀ ና ለታጠቀ ሕዝብ ትግል" ከቶ የማያፈገፍግ መሆኑን ያረጋገጠበት ጉባዔ ነው::

## መግቢያ

ባለፉት ስስት ዓመታት በተካሄደው ትግል የጠላትና የወዳጅ ሰፈር እየለየ ሄደ ትግሉም እየከረረና እየረቀቀ መጥቷል:: የኢትዮጵያን አብዮት የተለየ የሚያደርገው ፈጣን ሂደት ያለው መሆኑና እስከ ዛሬ ሰፊው ሕዝብ የተደጋጋቸው ድሎችም እዲሞክራቲክ አብዮትን እንጉ ሊያደርሰው የሚችለው እውነተኛ የወዝ አደር ፓርቲ /ከዚህ ፓርቲ ሌላ ማንም ግቡን ሊያስመታው አይችልም/ ባይ መሠረት በመሆኑ በንዳንዱ ወቅት የአብዮቱ ሠፈር ጠላቶችን ሲያጠቃ በሌላ ወቅት ደግሞ የአብዮቱ ሰፈር ወደ ኋላ እያሽገሸገ ሲከላከል ይታያል:: እሁንም የዚህ የወዝ አደር ፓርቲ መፈጠር አንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑን ጠቀኛ ተራማጆች ሁሉ ተረድተው ይህንኑ ፓርቲ መመሥረት ያለተቀጠበ ተጋድሎ አድርገዋል እያደረጉም ናቸው:: ሆኖም ተራማጆች በጠራ በወዛደሬ ርአዮተ ዓለም ተሰማምተው ወደ ውህደት የሚያመራቸው መንገድ እንዳይቀይሩ በመሃሉቸው ቅራኔዎች እንዳሏቸው ማንም የሚያውቀው ነው:: ይህም ቅራኔ በይፋ ከሰፊው ሕዝብ ፊት እንዳይፈታ ዲሞክራሲ አልተለቀቀም:: በተለይም "የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ" በማለት ጠቀኛ ተራማጆች ሲያስተጋቡ የቆዩት እንዲሁ ለይስሙላ አይደለም::

የዲሞክራሲ መብት ለጭቁኖች ማለት አብዮት ለመጣላቸው ወገኖች መሣሪያ ለማድረግና አብዮቱን ለማራመድ ነው:: በዚህ አኳኋን የኢትዮጵያን አብዮት ከግቡ ለማድረስ የአብዮቱን ጠላቶች ነጥሎ ለመምታትና የአብዮቱን ወዳጆች ለመሰብሰብ ያስችላል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በ1966 ዓ.ም. ሲፈነዳ ገብታዊ መልክ ነበረው ለኢትዮጵያም አዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት አስፈላጊ መሆኑን በሀገር ውስጥ ያሉ ተራማጆችና በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ሲታገሉለትና ሲሰውለት የቆየው የሰፊው ሕዝብ ጥያቄ ሆኖ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ወጣለት:: ይህም አዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ግቡ የሚደርሰው በነፃ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝብ ትግል ዓመፅ መሆኑን ሐቀኛ ተራማጆች የሚያምኑበትና የሚታገሉለት ነው:: ስለሆነም ለማንቃት ለማደራጀት ለማስታጠቅ ዲሞክራሲያዊ መብት አስፈላጊ ነው::

ትግላችን ቁጥር 2 ሰኔ 68 ገጽ 15 ሲጽፍ "የመደራጀት ዓላማ አብዮታውያን የሆኑትን መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ቁንጮዎች ሳይሆን በአጠቃላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አባሎችን በሙሉ ልብ ከትግል እንዲገቡ ለማድረግ ነው:: የዲሞክራሲ የትግል መሣሪያነት የሚታየው እዚህ ላይ ነው::

ይህ ተሳትፎ ሊገኝ የሚችለው አስቀድሞ እያንዳንዱ አብዮታዊ መደብ ወይም የህብረተሰብ ክፍል ዲሞክራሲያዊ በሆነ ውይይት ጥቅሙ ነው ብሎ የሚለውን አንጥር ማወቅ ማሳወቅና ለሱም መታገል የሚያስችለው የሚያምነው ድርጅት ሲኖረው ብቻ ነው" ብሎ ነበር::

ተራማጅ ድርጅቶችም ባሏቸው ቅራኔዎች እንዳይሸከሙት የዲሞክራሲ መብት ቢለቀቅ ልዩነቶቻቸው በይፋ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ቀርበው ዲሞክራቲክ በሆነ ዘዴ በተፈታ የወዝአደሩን ፓርቲ ለመፍጠር የሚደረገው ትግል በይበልጥ እየገፋና እየሰመረ በሄደ ነበር:: ሆኖም የኢትዮጵያ ሐቀኛ ተራማጆች የፈለገውን ያህል መስዋዕትነት ቢጠይቅ ይህን አንገብጋቢ የሆነውን የሰፊው ሕዝብ የዲሞክራሲ ጥያቄ በሥራ ላይ እንዲውል ከመታገል አይቆጠቡም::

ሰፊው ሕዝብ እስከ ዛሬ ያገኛቸው ድሎች በቀላል የሚገመቱ አይደሉም:: ሰፊው ሕዝብ የቀኝ ክንፍ ደንፊ ንዑስ ከበርቴ ይነዛው የነበረውን ቀልባሽ ፕሮፓጋንዳ ፓለቲካ ይዘት ገብቶት ለ"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት"ሳይሆን ነቅቶ ተደራጅቶ ታጥቆ በአመጽ ለሚያገኘው ለራሱ መንግሥት ሲታገል ብዙ ዕንቅፋቶችን እያለፈ እየወደቀና እየተነሳ ነው:: ወዝ አደሩ ባደረገው ውጣ ውረድ የተሞላበት ትግል የንዑስ ከበርቴውን ውቸንበር ተወጥቶ የራሱ የሆነ የሞያ ማህበር መ.ኢ.ሰ.ማን አቋቁሟል:: ሆኖም ፀረ አብዮተኞች ወዝ አደሩ በከረረ ትግል ያቋቋመውን ማህበር ለማዳከም ብዙ ሴራዎች ይጠነስሱበታል:: ጓድ ቴዎድሮስ በቀለን የመሰለ ታጋይ ጓድን ገድለውበታል:: ነገር ግን መ.ኢ.ሰ.ማ የጓድ ቴዎድሮስን አርአያነት በመከተል ከግራም ሆነ ከቀኝ ንዑስ ከበርቴ አድርባይነት የሚሠነዝርበትን



የርእዮተ ዓለም ብረዛ ተቋቁሞ ለወዝአደሩ መደብ እውነተኛ ሚናውን እንዲጫወት ተራማጆች ከወዛደሩ ጎን ቆመው ከመታገል ችላ አይሉም::

አርሶ አደሩም ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በፊውዳሊዝም ቀንበር ተይዞ ለራሱ ሳይሆን ለባላባቶች እያመረተ በረሀብ በችነፈር ሲሰቃይ ኖሮ በሰፊው ሕዝብ ትግል በተገኘው በታሪካዊ የመሬት አዋጅ "መሬት ላራሹ" ሆኗል:: ሆኖም ባለፉት ባይ ተንጓይነት ጥቅማቸው የተነካባቸው ባላባቶች አዋጁ ሥራ ላይ እንዳይውል በገጠሩ ቢሮክራሲና በጠር ትግል ከፍ ያለ ዘመቻ ቢያካሂዱበትም ከሞላ ጎደል በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ አዋጅ ጥሩ ውጤት እየሰጠና በአንዳንድ ሥፍራ ወደ ገጠር አብዮት እየተቀየረ ነው:: ዘማቾች በዚህ ጉዳይ ያደረጉት አስተዋጽኦና መስዋዕትነት ታሪክ ለዘለአለም ሲያስታውሳቸው ይኖራል::

የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያደረገውም አዋጅ ሌላው የአብዮቱ ድል ሲሆን በዚህ የተነሣ ጥቅማቸው የተነካባቸው ወደ ፀረ አብዮቱ ሰፈር ይበልጥ እንዲያሰፈስፉ አድርጓል:: ታላላቅ ነጋዴዎችን ይህ አዋጅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የነካቸው በመሆኑ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በበለጠ በኢኮኖሚ አሻጥርና በጥቁር ገበያ እንዲሰማሩ ሆኗል::

በንዑስ ከበርቴው በኩል የሚታየው ሁኔታ ግን እንደ መደብ ጠባዩ የተቸጉረጉረ ነው:: መሃል ሰፋው አብዮቱ ባያስደስተውም ሂደቱን እስካሁን ይከተላል እንደጊዜው አመችነትም የተራማጅ ካባን ለማጥለቅ ይሞክራል:: ቀኝ በኩል የተሰለፈውም ኢ.ህ.አፓ ግልጽ የሆነ አድሃሪ አቋሞች በመውሰድ ባይወስን ወደ ነፍስ ገዳይነትና ወደ ነጭ ሽብር አልፍ ሰፊው ሕዝብ ተፋቶታል::ዘምቶበታል::

አዲስ ዲሞክራቲክ አብዮት ያለ ሴቶች ተሳትፎ አይሰምርም:: ሴቶች በአሁኑ ጊዜ ያለባቸውን ድርብ ጭቆና በታጋይ ተራማጅ ሴቶች አማካይነት በተደረገው ቅስቀሳና ትግል ለእኩልነት ለፍትህና ለብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የሚታገሉ ብዙ ናቸው:: በትግላቸውም የቀኙን ንዑስ ከበርቴ ሴራ በርእዮተ ዓለም አሸንፈው ከብዙ ትግል በኋላ በቅርቡ "ኢ.ሴ.አንን" ማቋቋማቸው የአብዮቱ ሌላው ድል ነው::

የኢትዮጵያን አብዮት በአሁኑ ጊዜ ለቀለበሳ ከሚያመቹት ሁኔታዎች አንዱ የቢሮክራሲው ተቋም እንደለ መቆየትና በደርግም በኩል ከቢሮክራሲው ጋር በየጊዜው የሚታየው መቀራረብና አብዮቱን ከፊውዳሊዝም በተወረሰው ቢሮክራሲ እስከ ሄደበው የሚለው ፍጹም ፀረ አብዮታዊ አስተሳሰብ ነው:: ይህ የተወረሰው የተገማማ ቢሮክራሲ አስድሃሪው የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በሚያመች ሁኔታ ለቢሮከበርቴዎችና ለኢምፔሪያሊስቶች መሆኑ ሲታወቅና በይፋ በየጊዜው የሚያደርጋቸው አሻጥሮች፣ ሃቀኛ ተራማጆችን የማሠር፣ ከሥራ የማስወገድ፣ የማስገደል ...ሲታወቅ ሃቀኛ ተራማጆች ደርጉ ከርሱ ጋር የሚያደርገው መቀራረብ በስልጣን ላይ የመደላደሉን፣ አብዮት የመቀጨቱን፣ የመደብ ትግል የማፈንን ምኞቱን ያንጸባርቃል የሚሉ ግምቶች እንዲወስዱ ያስገድዳቸዋል:: በተለይም ሃቀኛ ተራማጆች የታቀደው ዘመቻና ሕዝባዊ ሠራዊት "አብዮታዊ አመራር ይኑረው" "ቢሮክራሲው እያዘምት ይዘመትበት" "ህዝባዊ ሠራዊት ለነፃ ለተደራጀ ለታጠቀ ለሰፊው ሕዝብ

ትግል" እያሉ በሚጮሁበት ወቅት እንደሚታየው ቢሮክራሲው እያዘመተ ነው::

የኢትዮጵያ አብዮታውያን ደጋግመው ደጋግመው ለሰፊው ሕዝብ የሚያስተምሩት ሃቅ በሃገራችን ላይ የደረሱ ችግሮች መፍትሄ የሚገኝላቸው ከአብዮቱ ትግል መገፋት ጋር የተያያዘ መሆኑን ብቻ ነው:: አብዮቱም ውጣ ውረድ የተሞላበት ጉዳና ቢሆንም ሌላው ጠቀ ደግሞ አብዮቱ ግቡን የሚያስመታው ሰፊው ሕዝብ "ከራሱ ተማምኖ በጠራዊ ነፃነትን ላለማስደፈር የውጭ ሃይሎችን እንደ ድጋፍ እንጂ ወሳኝ" አድርጉ ሳይቆጥር ነቅቶ ተደራጅቶና ታጥቆ በኢምፔሪያሊዝም በፊውዳሊዝምና በቢሮክራሲ ካፒታሊዝም ላይ ዘምቶ ሲደመስሳቸው ብቻ ነው:: ዛሬ አብዮቱ ከውስጥና ከውጭ በፀረ አብዮት ኃይሎች በመብርበር ላይ በሚገኝበት ወቅት የጊዜው ዋነኛ ቅራኔ የውስጥና የውጭ ጠላቶች በጥምር ባንድ በኩል በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሌላ በኩል ያለው ቅራኔ መሆኑን እንገነዘባለን:: ስለሆነም የውስጥና የውጭ ጠላቶቻችንን ለያይተን ተመልከተን አንዱን ዛሬ አንዱን ነገ የምንዋጋው ሊሆን አይችልም:: ጠቀና ተራማጆችም የቅራኔውን ምንነትና የሚፈታበትን አብዮታዊ መንገድ ለሰፊው ሕዝብ በማስተማር እስከዛሬ የተገኙትን ድሎች ላለማስነጠቅ ከሰፊው ሕዝብ ጎን ሆነው በግንባር ቀደምትነት መሰለፍ አብዮታዊ ግዳጃቸው ነው:: የኢትዮጵያን ጊዜያዊ ሁኔታ ስናጤነውና ባሁኑ ጊዜ በደርግ በኩል የሚወሰዱትን እርምጃዎች ስናይ አዘማሚያቸው በውጭው ጠላት ላይ ብቻ ያተኮረ ሆነው እናገኛቸዋለን:: ስለዚህ አብዮቱን ከውስጥ ለማስቀልበስ አመቺ ሁኔታ መፍጠሩን መረዳትና ይህን ስህተትና አቋም መታገል የጠቀና ተራማጆች ተግባር ነው::

ለማጠቃለል ያህል፣ 17ኛው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔያችን በተካሄደበት ወቅት ቁልጭ ብሎ የታየው የኢትዮጵያ ሁኔታ የውጭ ኢምፔሪያሊዝምና የውስጥ አድኃሪዎች ባንድ ወገን፣ ሰፊው ሕዝብ ደግሞ በሌላ ወገን ሆነው በነዚህ በሁለቱ መሃል ያለው ቅራኔ ዋነኛ ቅራኔ መሆኑና የትግል ታክቲክ በምንቀይስበት ጊዜም ከዚህ እንፃር ተነስተን መሆን እንደነበረበት ነው::



## የ17ኛው ጉባዔ አካሄድ

በጉባዔው ላይ የተገኙት ቅ/ማህበራት 13 ሲሆኑ የጉባዔው ተካፋይ ከ180 እስከ 200 የሚደርስ ነበር:: በጉባዔው ላይ የተገኙት የቅርንጫፍ ማህበራት የሚከተሉት ነበር::

1/ ቤልጅየም /2/ እንግሊዝ /3/ ምዕራብ ጀርመን /4/ምስራቅ ጀርመን
5/ ፊንላንድ /6/ ፈረንሣይ /7/ ኖርዌ /8/ ሶቪየት ሕብረት
9/ ቡልጋሪያ /10/ ሃንጋሪ /11/ ቼኮዝሎቫኪያ /12/ ዩጎዝላቪያ
13/ ስዊስ፣ በግለሰብ ደረጃ ከዴንማርክ ፣ በተጨማሪም አምስቱን ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች የወከሉ ሁለት ጓዶች ከአዲስ አበባ ተገኝተዋል::

በ7/8/77 ማታ የቅ.ማ.ወኪሎች፣ የአ.ኢ.ተ.ማ. ሥራ አስኪያጅና የመጽሔት ቦርድ ስለጉባዔው አካሄድ ስለአጀንዳውና ስለ ፀጥታው ጉዳይ ተነጋገረው በሰበሰባው ከሞላ ጎደል በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የተዘጋጀውን አጀንዳ አፀደቁ:: ባሁኑ ዓመት በአድኃሪ ጥይት ተመትቶ ለወደቀው ለጓድ አብትላሁ ፀሐዩ ይህ የ17ኛው ጉባዔ መታሰቢያ ይሆን ዘንድም ተስማማ::

በ8/8/77 በ4ሰዓት ላይ የአኢተማ ሥራ አስኪያጅ ፕሬዚዳንት ንግግር ከማድረጉ በፊት በአድኃሪያን ጥይት ለወደቀው ለጓድ አብትላሁ ፀሐዩና የሌሎች ታጋዮችንም ተጋድሎ በማስታወስ ለአንድ ደቂቃ ፀጥታ የጉባዔውን ተካፋዮች ጠየቀ:: መራራው ትግል የተሰኘው አብዮታዊ መዝሙር ተዘመረ::

የማህበሩ ፕሬዚዳንት ስለ ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሁኔታና በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ ላይ የመክፈቻ ንግግር በማድረግ የ17ኛውን ጠቅላላ ጉባዔ ከፈተ፣ የዓለም አቀፍ ሁኔታን በተነተነበት ጊዜም ስለ ቻይናው ሊቀ መንበር ማኦ ዕረፍት ጉባዔው ሐዘኑን በአንድ ደቂቃ ፀጥታ ገለጸ::

ንግግሩ እንዳበቃም ከልዩ ልዩ ድርጅቶች የአንድነት መግለጫዎች ተሰሙ:: የአንድነት መግለጫ ያሰሙ፣ የላኩና እንዲሁም በቴሌግራም ያስታወቁ የሚከተሉት ነበሩ::

1. በቻይና የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ማህበር
2. የተባበሩ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች አንድነት ማህበር በሰሜን አሜሪካ
3. በካይሮ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
4. በካናዳ ከሚገኙ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን /ሞንሪያል/
5. በሱዳን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
6. በአውሮፓ የኢትዮጵያ ሴቶች ዲሞክራቲክ ማህበር
7. በአውሮፓ የኦሮሞ ተማሪዎች ማህበር.(TIBOBA)
8. በሎስአንጀለስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ጥናት ክበብ
9. የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /ኢትዮጵያ/

10. ከምስተ የማርክሰስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ሕብረት /ኢትዮጵያ/
11. አዲስ ፋና /ኢትዮጵያ/
12. International Student Organization - Leuven Belgium
13. The Political Bureau of the Communist Labour Party - USA
14. Union des Etudiants Centre Africains - Paris
15. Lesotho Students Union - Czechoslovakia
16. Sveriges Kommuntstiska Undomsforbund (ML) - Goteborg
17. Irish Republican Movement International Affairs Bureau - Ireland
18. Mozambique Students in Czecoslovakia
19. Angolan Students Union in Czecoslovakia
20. Namibian Students Union in Czecoslovakia
21. Federation of Unions of African Students in Czecoslovakia
22. Uganda Students Union in Czecoslovakia
23. Humanité Rouge - Paris
24. Union des Populations du Cameroun
25. African Club in Czecoslovakia
26. Organization Demokratischer Studenten und Jugend Irans
27. Irish Democratic Youth Movement - Ireland
28. International Union of Students
29. Svenska Fredskommitten - Sweden
30. Dahomey Students Union in Belgium
31. FOPAL - Belgium
32. Frelimo's Students in Czechoslovakia
33. Anti-imperialist Solidarity Committee of FRG
34. በግለሰብ ደረጃም ከተለያዩ ቦታዎች ቴሌግራምና ያንድነት መግለጫዎች ተነበዋል::



በዚሁ አለት ጥዋት የሊቀ መንበር፣ የፀሐፊዎችና የኦዲተሮች ምርጫ እንደ ተከናወነ በቤተ ውስጥ እንደ የሁኔታው የሰዓት ማሸጋሸግ እንዲደረግ በምምነት ተደረሰ::

<u>የአሲታማ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሪፖርት</u>

በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሊቀመንበር አማካይነት በላከናወናቸው ሥራዎችና በኢትዮጵያ ዝዜያዊ ሁኔታ ላይ በለወሰዷቸው እቋሞች በሩ ያለ ማብራሪያ የያዘ የአመቱ ሪፖርት ተነበበ:: የሪፖርቱም ዋና ዋና ይዘት፣

- የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ባመቱ በለተከታተለው ፖሊሲ፣
- ባመቱ ውስጥ በለተደረገው የሁለት መስመር ትግል፣
- በ1965ው ጉባዔ በሰጠው ኃላፊነት ባለም ዓቀፍ በለመደራጀት፣ ከመካከለኛው ምስራቅና ከሌቀ ሌቀ ድርጅቶች ጋር በለነበረው ግንኙነት
- ከቀ/ማህበራት ጋር በለነበረው ግንኙነት፣ በተለይም ባሁኑ ዓመት በፊንላንድና በምስራቅ ጀርመን ማህበር መቋቋሙን የሚያብራራ ይገኙበታል::

በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሪፖርት ላይ በሩ ያለ ጭውውት ውይይት ተካሄደ አስፈላጊው ማብራሪያ ከተሰጠበት በኋላ ያለ ምንም ተቋዋሚ በጋለ ጭብጨባ ቤቱ ተቀበለው:: በአጀንዳው መሠረት የአሲታማ መጽሔት ቦርድ ሪፖርት ተነበበ::

<u>የአሲታማ የመጽሔት ቦርድ ሪፖርት</u>

የዚህም ሪፖርት ይዘት፣
- ዘጠኝ መጽሔፍ ማውጣቱን /4 ትግላትን ዜና፣ 3 ትግላችንና 2 ታጠቀ/
- በተለይ ባሁኑ ዓመት ጸሐፊዎች በደበለጥ የተገኙት ከጠገር ቤት መሆኑን
- ከጠገር ቤት የሚመጡትን "ነፃ ጋዜጦችና" ጠቃሚ የሆኑ ጽሑፎች ከአዲስ ፋና"ና ከአገር ቤት ጋዜጦች ማውጣቱን፣
- በተለይ ወደ ምሥራቅ አገሮች በሚላኩ ጽሑፎች/በተለይ ሀንጋሪ ሶቪየት ሕብረት/ ችግር እንደተፈጠረና መፍትሔውን ቤቱ እንዲፈልግላቸው ለቤቱ አቀረበ::
- መጽሔት ቦርዱ የገንዘብ ችግር በጣም እንደነበረበትና ዕዳ ይዞ መምጣቱንም ለቤቱ ገለፀ::

ማታ " ያለፈው ሸክም፣ የወደፊቱ ጉዳና " የሚባል ፊልም ታየ::"

በ9/8/77 ጥዋት የመጸሔት ቦርድ ሪፖርት ላይ ውይይት ተደርጎ ቤቱ ሪፖርቱን በሙሉ ድምጽ ተቀበለው::

ከቀትር በኋላም በጉባዔው የተወከሉት የ13 ቀ/ጣ. ሥራ.አ.ኮሚቴዎች በየተራ ሪፖራቸውን አቀረቡ፤ ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታ፣ በሚገኙበት አገር ስላጋጠሟቸው የድርጅት ነክ ጉዳዮችና ስላደረጉት የሁለት መስመር ትግል አብራርተዋል::

ማታ፣ አምስቱን ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ወክለው የመጡት ሁለት ጓዶች ስለህብረቱ ሁኔታ፣ ስለ ተራማጅ ቡድኖች አንድነት፣ ስለቀራኒዎቻቸው፣ ስለኢትዮጵያ ሁኔታ ሰፋ ያለ ውይይት ተካሄደ አንዳንቃ ስለ <u>ሜይ ዴይ ፊልም</u> ታየ:: በዚህም ፊልም "ኢሰፓን ምን ያህል ከሕዝብ ጋር እንደተዋሃደ ተሳታፊዎች ሊገነዘቡት ችለዋል:: ኢሰፓንን አርማ የያዙ ጓዶች በፊልሙ ውስጥ በሚታዩ ጊዜ የጉባዔው ተሳታፊዎች የጋለ ጭብጨባ ያደርጉ ነበር፤ እንዲሁም የሌኒን የስታሊንን ፎቶዎች የነጓዱ ፍቅረን ና የሌሎች ታጋይ ጓዶች ፎቶዎች የያዙ ጓዶች በሚታዩ ጊዜ ቤቱ ከፍ ያለ ጭብጨባ አስተጋብቷል::

<u>ከ10/8/ እስከ 11/8/77 የኮሚሽን ጥናት፣</u>

በ10/8/77 አባላት በሰበት ኮሚሽኖች በመከፋፈል ስለኢትዮጵያ ጊዚያዊ ሁኔታ ውይይት ማድረግ ጀመሩ:: ለመንደርደሪያ የቀረቡት ጥናቶች የሚከተሉት ነበሩ፣

1/ <u>ስለ ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት</u>
   ሀ/ ምንነትና ግብ
   ለ/ አካሄዱ ስለወዛደር ፓርቲ
2/ <u>የኢትዮጵያ ጊዚያዊ ሁኔታ</u>
   ሀ/ የሰሜኑ ሁኔታ
   ለ/ የደቡብ ሁኔታ
   ሐ/ የመሐል ሁኔታ
   መ/ ያካባቢ ሁኔታ
   ሠ/ የኢኮኖሚ ሁኔታ
   ረ/ የኃይሎች አሰላለፍ

3/ <u>ጊዚያዊ ወ.መንግሥትና የኢትዮጵያ አብዮት</u>
   ሀ/ የደርግ መደባዊ ይዘት
   ለ/ ጊ.ወ.መንግሥትና የዲሞክራሲ ጥያቄ
   ሐ/ ጊ.ወ.መንግሥትና ዘመቻው
   መ/ " " " አሰባ



   ሠ/ ጊ.ወ.መንግሥትና ቢሮክራሲ
   ረ/ አብዮታዊ ሄሰ ስለሚለው መፈክር
   ሰ/ የውጭ ዐርዳታ ጉዳይ

4/ <u>ስለ ብሔር ጥያቄ</u>

   ሀ/ ስለ ኤርትራ
   ለ/ ስለ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች
   ሐ/ ስለ ተገንጣይ ቡድኖች

5/ <u>ስለ ተራማጆች ተግባር</u>
   ሀ/ ስለ ልዩ ልዩ ተራማጅ ድርጅቶች
   ለ/ ስለ ተራማጅ ድርጅቶችና ስለወዛደር ፓርቲ
   ሐ/ ተራማጆችና ሕዝባዊ ድርጅቶች

ይህ የኮሚሽን ጥናት እስከ 11/8/77 ድረስ ተካሄደ:: ሰበቱ ኮሚሽኖች ከፍተኛ አብዮታዊ ስሜት በተሞላበት አኳኋን በጥናቱ ልዩ ልዩ ነጥቦች ላይ ውይይትና የሃሳብ ለውውጥ አድርገዋል:: በተለይም በዚህ በ17ኛው ጉባዔ ከአገር ቤት የተገኙት የአምስቱን የማርክሲስት ሌኒኒስት "ሕብረት" ወክለው የመጡት ሁለት ጓዶች በየኮሚሽኑ እየተዘዋወሩ ገለጻዎችና ቀጥታ ኢንፎርሜሽን በመስጠታቸው ጠቃሚ ትምህርቶች ሊቀሰሙ ተችሏል::

በ12/8/77 ጥዋት የኮሚሽን ጥናቶች ተገባደው እንዳለቀ የየኮሚሽኑ ሊቀመናብርት የኮሚሽኑን የሁለት ቀን ውይይቶች ዋና ዋና ይዘቶች ለጠቅላላ ጉባዔ አቀረቡ በየኮሚሽኑ ከተነሱት ዋና ዋና ጥያቄዎች የሚከተሉት ይገኛሉ::

- በተለይ ስለ በራስ መተማመንና ስለ ብሔራዊ ነፃነት ጉዳይ
- ስለ "ዐርዳታ ድጋፍ እንጂ ሠሻግ አይሆንም" ስለሚለው መርሆ
- ስለ ቢሮክራሲ
- ስለ ዲሞክራሲ መብቶች
- ስለ ዘመቻው
- ስለ ድርጅት ጉዳይ፣ እነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ ከ12/8/77 እስከ 13/8/77 እንደበላሉ ተደረጉ::

በ14/8/77 ጥዋት የውይይቱን ዋና ዋና ነጥቦች የሚያጠቃልለው የውሳኔ ረቂቅ ለጉባዔው ቀረበ:: በሩ ያለ ውይይት ተደርጐ ውሳኔው ላይ ማሻሻያዎች ቤቱ በጠየቀው መሰረት ተደርጎባቸው ውሳኔው ተቀናብሮ ለቤቱ ለመጨረሻ ጊዜ ቀርቦ ተነበበ:: ውሳኔውም ድምፅ ተሰጥቶበት ያለአንዳች ተቃውሞ ይህን የ17ኛው የኢ.ተ.ማ ጉባዔ መመሪያ ውሳኔ ቤቱ ሙሉ በሙሉ በጋለ ጭብጨባ አፀደቀ አብዮታዊ መዝሙሮች ተዘመሩ::

የኦዲተር ሪፖርት በዚሁ ቀን ተነበና ውይይት ተደርጎበት በጭብጨባ ፀደቀ:: የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ምርጫ ተካሄደ በዚሁም መሰረት የበፊቱን ቀ/ማህበር ሥራ አስኪያጅን እንደገና እንዲወስዱና ያለፈው ዓመት መጽሔት ቦርድ የዚህን አመት በድጋሚ እንዲወስዱ በቤቱ በቀረበው መሠረት የፈረንሣይ ቀ/ማህበር ኃላፊነቱን ተቀበሉ:: የአዲሱ ተመራጭ ሥራ አስኪያጅ ሊቀመንበር ጉባዔውን ለመሩ ጓዶች ምስጋና ካቀረበ በኋላ ዓለም ዓቀፍ ተዘምሮ የ17ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ፍፃሜ ሆነ ማታም የመለያያ ምሽት ተደረገ::



በሎዛን ከተማ ከ7/8/77 እስከ 14/8/77 የተሰበሰበው በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ያሳለፈው የፖለቲካ ውሳኔ

---

## የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ከየካቲት እስከ ዛሬ የሚያካሄዱትን ትግል በየካቲት 1966 ከጀመሩ ወዲህ የተጓዙት አብዮታዊ ጉዳና እጅግ ጠመዝማዛና ውጣ ውረድ የበዛበት ጉዳና ነበር::ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከየካቲት ወዲህ ባካሄደው ቆራጥ ተጋድሎ በታጋይ ልጆቹ ደምና መስዋእትነት የተቀዳጃቸው ብዙ ድሎች አሉ::በዚህ ትግል ውስጥም በንቃት፣በድርጅትና በተጥቀ ተራምደ፣ከትግሎም ብዙ ትምህርቶችን በመቅሰም ለመጭው ትግልና ለሌሎች አዳዲስ ድሎች ከመቼውም የበለጠ ዝግጁ እየሆነ መጥቷል::በነዚህ ዓመታት የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ነፃነትና አንድነት ጠላቶችም አብዮታችንን ከፉኛ ተፈታትነውታል:: ብዙም ጥቃት አድርሰውበታል::አያሌ ገበሬዎች፣ወዝአደሮች፣መለዮለባሾች፣ወጣቶች፣ሴቶች፣አብዮታዊ ምሁራንና መኮንኖች ከፀረ አብዮት ሃይሎች ጋር ሲተናነቁ በየቦታው ወድቀዋል:: ነገር ግን በአብዮታችን ላይ ከጠላቶች የተሰነዘረው ጥቃት፣በዚህ ጥቃት በግፍ የፈሰሰው የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ደም ሰፊውን ሕዝብ በአብዮቱ ይበልጡን እንዲገፋ ቀሰቀሰው እንጂ ከትግል ሜዳ እንዲያፈገፍግ አላደረገውም::ስለዚህ አብዮታችን እስከዛሬ ሳይቀለበስ ሊቆይ ችሏል::

1969 በኢትዮጵያ አብዮት ታሪክ ውስጥ የብዙ ትግሎችና የብዙ ድሎች፣የብዙ መውደቆችና የብዙ ትምህርቶች ዓመት ሆኖ ተመዝግቦ ይቆያል:: ይህ ዓመት፣እየወደቁ እየተነሳ በመካሄድ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ትግል ሰበተኛ ዓመቱን የያዘበት፣ከፍተኛ ትግሎች የተደረጉበት፣አያሌ የፖለቲካ ድሎች የተገኙበት፣ፀረ አብዮት ሃይሎች ከሰፊው ሕዝብ ተነጥለው ለብቻቸው የተሰበሰቡበት፣እንደ ኢህአፓ ያሉ አድሃሪ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ተጋልጠው በሰፊው ሕዝብ በመተፋት ከጠላት ሰፈር በግልጽ የተቀየጡበት፣የአብዮቱ ወገኖች ደግሞ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ጥራት ባለው ሁኔታ ያሉበትን አቋም ተረድተው ለወሳኙ ድል መዘጋጀት እንዳለባቸውና ምን ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸው እየተረዱ የመጡበት ዓመት ነበር::ይህ ዓመት የፀረ አብዮት ኃይሎች በውስጥና በውጭ ተጠናከረው በይፋና በሰውር በጥቃትና በተዘዋዋሪ መንገድ እየደጋገሙ

በአብዮቱ ላይ ያመጹበት፣አብዮታችንንም ከፍተኛ አደጋ ላይ የጣሉበት፣የአብዮቱ ሃይሎች ትግላቸውን በተወሳሰበ ሁኔታ በመቀጠል ብዙ መከራና ስቃይ የተቀበሉበት ዓመት ነበር::ባጭሩ 1969 የአብዮትና የፀረ አብዮት ሃይሎች ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ጥራት ባለው ሁኔታ በየሰፈራቸው እየተሸገሹ ሄደው ጊዜያዊ ማጥቃትና መከላከል በሁለቱም ሰፍሮች እየተፈራረቁ መራራ ትግል የተካሄደበት ዓመት ነበር::በ1969፣የተካሄዱት ትግሎች አብዮትንና ፀረ አብዮትን ወደ ወሳኙ ፍልሚያ አቀረቡ እንጂ የአንደኛውንም ዘላቂ ድል አላበሰሩም:: ዛሬም፣እንደአምናው ሁሉ የኢትዮጵያ የአብዮትና የፀረ አብዮት ሃይሎች አለተሸናነፉም::ሁለቱም ለተቃራኒ ግብ ተመሳሳይ ዝግጅታቸውን በማፋጠን ላይ ናቸው::

የ1969 መጀመሪያ በኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆች የከረረ የርእዮተዓለምና የፖለቲካ መስመር ትግል የተገኙት ከፍተኛ የፖለቲካ ድሎች በማረጋገጥ ተከፈተ::ሰፊው ሠርቶአደር ከወዥንብር ወደ ጥራት፣ከቀለባሽ መሥመር ወደ አብዮታዊ መሥመር መሸጋገሩን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ተፈጠሩ::ሰፊው ሠርቶአደር የለየላቸው የቀድሞ ጠላቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በአብዮቱ ሂደት ውስጥ ተንሸራተው ፀረ አብዮት ሰፈር የወደቁት ግን ወዳጅ መስለው ያስጠቁት ሰርጎ ገብ አድሃሪያች ላይ ተነሳ::በወዥንብር ውስጥ እያለ ለእነርሱ አስረክቦቸው የነበሩትን ሕዝባዊ ድርጅቶችን ከሰርጎ ገብ አድሃሪያች አፈልቅቆ እያወጣ በራሱ ቁጥጥር ስርና የራሱ መገለገያ አደረጋቸው::በዚህም መሠረት የሰርጎ ገብ አድሃሪያች መገለገያ የሆነ የወዝአደሩ ቅዮ ማህበራት፣ የከተማ ሠርቶአደሮች የቀበሌ ማህበራትና ሌሎችም ሕዝባዊ ድርጅቶች የተራማጆች፣የጭቁኖችና የነቃ ሠርቶአደሮች አመራር አገኙ::ባንድ ቃል ሰፊውን ሕዝብ ተደባልቀው ውስጥ ውስጡን ትግሉን በርቡረው ለማዳከም የተሰለፉ አድሃሪያች በፖለቲካው መስክ መሸነፋቸው ገለጽ ወጣ::

ከዚህ መሸነፍ በሃላ ኢህአፓና ሌሎችም አድሃሪያች ከንግዲህ የሰርጎ ገብነታቸው ዘመን እያከተመ መሄዱን ተገንዝበው የሰፊውን ሕዝብ ንቃትና ድርጅት ለማፈንና እድገቱንም ለማገድ ታክቲክ ለመለወጥ ተገደዱ::ይህም አዲስ ታክቲክ በሰፊው ሕዝብ ሰፈር ሽብር መፍጠር፣ይበልጥ እንዳይነቃ አንቂዎችን መግደል፣ይበልጥ እንዳይደራጅ ያሉትም ድርጅቶች እንዲበተኑ፣የሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎችን እያሳደዱ መረሸን፣አጣጥር እንደለብ እንዲሰራ ተራማጅ የመንግሥት ሠራተኞችን መግደል፣ማዛወር፣ከሥራ ማባረርና በመሳሰሉ ይፋ በሆኑ ፀረ ሕዝብና ፀረ አብዮት ድርጊቶች የተገለጸና የሚገለጽ ታክቲክ ነበር::የአብዮቱ ሰፈር የተቀዳጃቸውን የፖለቲካና የርእዮተዓለም ድል ለማስጠበቅና ለማጠናከር የሚያስችለው የትጥቅ ሃይል አልነበረውም::አድሃሪያች የጀመሩበትን ነጭ ሽብር ለመከት ባለመቻሉም ከፍተኛ ጥቃት ሲደርስበት በቅቷል::

በ1969 ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገኘው የፖለቲካ ድል በውስጥ ብቻ የተወሰነ አልነበረም::በዓለም አቀፍ ደረጃ፣በእምፔሪያሊስቶችና በጎረቤት



አድሃሪያች ፀረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ የተጧነበትን ብቸኝነት መሰባበር የያዘበት አመትም ነበር::በዚህን ዓመት የኢትዮጵያ አብዮት ከመቼውም የበለጠ ዓለም አቀፋዊ የሆነ የተራማጅ ሃይሎችንና መንግሥታትን ድጋፍ አገኘ::ባንፃሩ ደግሞ በአብዮቱ ስር መሰደድ የሰጋ በእንጭጩ ሊቀጩት ያደቡ ኢምፔሪያሊዝምና የጎረቤት አገር አድሃሪያች በኢትዮጵያ አብዮት ላይ የነበራቸው ተቃውሞ እያየለ ሄደ አብዮቱን ከበው ለማስጨነቅ ለውስጥ አድሃሪያች የቀለበሳ ተገን መሆን በይበልጥ ገፍተውበታል::

ይህም ብቻ አይደለም፣ የኢትዮጵያ አብዮት በውስጥ ፀረ አብዮተኞች መቦርቦሩ፣በውጭ ጠላቶች ተወጥሮ መያዙ የ69 የቀለበሳ ትግል አንድ ገጽ ነው::በሌላ ገጽ፣በደርግ ውስጥ አድሃሪ ሃይሎች የበላይነት አግኝተው አድሃሪውን ቢሮክራሲ ምርኩዝ በማድረግ ከፍተኛ ፋሺስታዊ መፈንቅለ መንግሥት ስራ ይተብትቡ ጀመር::እንደዚህም በአንድ በኩል እየነቃና እየተደራጀ የመጣው ሰፊ ሕዝብ የፖለቲካ ድሎችን በትጥቅ ሃይል እንዳያስከብር የትጥቅ ጥያቄውን በማፈን፣በሌላ በኩል አብዮቱን ከውስጥ ለሚቦረቡሩ ቀለባሾች ስልጣናቸውን ከለላ በማድረግ የፀረ አብዮቱን ሰፈር አጠናከሩት፣አብዮቱ መፈናፈኛ አጣ::የቀለበሳ አየር ከቅርቡ ይሸት ጀመር::

ይህም ሁሉ ሆኖ ግን ሰፊው ሕዝብ ለዚህ የአድሃሪያች መጠናከር አሳጉደደም፣የትጥቅ ጥያቄው መልስ እንዲያገኝ "ሰፊው ሕዝብ ይታጠቅ" በሚለው መፈክር ስር ትግል ቀጠለ::"ኢህአፓ አይሂድ ኢ.ኢስ.ኤፍ ይውደም" በሚል መፈክር ስር ጠላቶቹን ለመደምሰስ ያለውን ቁርጠኛነት ማሳየቱን ገፋበት:: "አድሃሪ መኮንኖችና ቢሮክራቶች ይውደሙ" ብሎ ከላይ በአብዮቱ ላይ የሚውጠነጠነውን ሴራ ማጋለጡን ቀጠለ::በዚህ ትግል ታግዞና ከሰፊው ሕዝብ ጉን በመቆም ተራማጅ የደርግ አባሎች ከደርግ ውስጥ ባሉት ቀንደኛ አድሃሪያች ላይ ቆራጥ አብዮታዊ እርምጃ በጥር 26/69 ሲወስዱ የተፋፋመው የቀለበሳ ከአናቱ ላይ ለጊዜው ተመታ::አብዮቱ አዲስ እስትንፋስ አገኘ::

በዚህ ምቹ ሁኔታ መፈጠር የሰፊው ሕዝብ የትጥቅ ጥያቄ መጠነኛ መፍትሄ ማግኘት ጀመረ::ኢዲዩን፣ኢህአፓንና ኢኢስኤፍን ለመደምሰስ ቆርጦ የተነሳው ሰፊ ሕዝብ በያለበት በሕዝባዊ ድርጅቶቹና በአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች አማካይነት ፀረ አብዮተኞችን ማራወጥ ያዘ::አድሃሪ ሃይሎችን ብርክ ባስያዘና የሰፊውን ሕዝብ ወገኖች አንደት ባራሱ ነፃ እርምጃዎቹ አያሌ ጠላቶችን ደምስሰ፣ብዙዎቹንም በቁጥጥሩ ስር አዋለ::የአብዮቱ አዲስ እስትንፋስ ማግኘትና ወደፊት መገስገስ በበኩሉ ባንድ ወገን የውጭ ጠላቶች አገራችንን ከበው አብዮቱን ከማስጨነቅ አልፈው ከውስጥ አድሃሪያች ጉን እንዲሰለፉ ሲያደርግ በሌላ በኩል ደግሞ የውስጥ አድሃሪያች፣በተለይም አድሃሪው ቢሮክራሲ በተለየ ታክቲክ ይህን የሰፊው ሕዝብ የወደፊት እርምጃ ለመግታት መራወጥ አስከተለ::

አብዮቱ ከጥቂት ሳምንታት የአጥቂነት ትግል በኋላ ብዙ መሰናክሎች ገጠሙት፡፡ "መንግሥት የለም እንዴ" ፣ "ሕዝቡ ሲጨረስ እኮ ነው" በሚል ፀረ አብዮት ፕሮፓጋንዳ የአድሃሪው ሠፈር የአብዮታዊያንን የማጥቃት እርምጃዎች ማጥላላት ሲጀምር አድሃሪው ቢሮክራሲ ይህችን ቀበል አድርጎ "ስነ ስርዓት ለማስከበር" በሚል ሰበብ የሰፊውን ሕዝብ ነፃ እርምጃዎች ማፈን ያዘ፡፡

ባጭሩ በአሁኑ ወቅት አብዮቱ ጠላቶችን እንዲያጠቃ ተፈጥሮ የነበረው ምቹ ሁኔታ በየካቲት—መጋቢት አካባቢ በነበረው መልክ አልቀጠለም፡፡ባንድ ወገን፣ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አድሃሪውን ቢሮክራሲ በመምታት ጥረት አልገፋበትም፡፡ ቀንደኛ አድሃሪዎች ከቢሮክራሲው አናት ላይ እንዲወርዱ አለመደረጉ፣በቢሮክራሲው ውስጥ አንዳንድ ቁልፍ ቦታዎች ከለሰው በአድሃሪያን መያዛቸው ይህንኑ ያመለክታል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ፣በዚህ የደርግ ክርክም መቀረት የለብ ለብ የተሰማው አድሃሪ ቢሮክራሲ የሰፊውን ሕዝብ ነፃና አብዮታዊ እርምጃዎች ለማቀዛቀዝና ለማደናቀፍ መቻሉ ሰፊው ህዝብ በጠላቶች ላይ ሊያደርስ ያቀደውን፣ወይንም የሚችለውን እንዳያደርግ አስቆሞታል፡፡

የዚህም ውጤቶች ባንድ በኩል የአድሃሪው ቢሮክራሲ እንደገና ማንሰራራት፣የከተማ ሽብር ፈጠራዎች እንደገና በሰፊው ሕዝብ ወገኖች ላይ የተፋፋመ ጥቃት ማድረስ፣በአድሃሪ የታጠቀ አመጽ አብዮቱን ለመቀልበስ የሚታገሉ ፀረ ሕዝብ ድርጅቶች ከኢምፔሪያሊዝምና ከጉረቤት አድሃሪዎች ጋር በይበለጥ በመተባበር የሚያካሂዱትን የታጠቀ አመጽ እንደገና ማባባሳቸው ነው፡፡ ስለሆነም ባሁኑ ወቅት ያለው የሃይል ሚዛን ለአድሃሪዎች የሚያደላ ነው፡፡ የውስጥና የውጭ ጠላቶች ከመቼውም ይበልጥ ተቀራርበው በአድሃሪው ቢሮክራሲ እየታገዙ የሚያካሂዱት የፀረ አብዮት ትግል ተጠናከረ እንጂ አልቀነሰም፡፡

ሀ/ <u>የሰሜኑ ሁኔታ</u>

ሰሜን ኢትዮጵያ፣የአገራችን አድሃሪዎች ተባብረው አብዮቱ ለመቀልበስ ተጠናከረው የሚገኙበት ክፍል ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ከመደብ ጥቅም አንጻር ከአብዮቱ ወገን ሊቆሙ የሚገባቸው ሃይሎች በንቃትም በድርጅትም በተጥቅም ወደ ኋላ የቀረበት ክፍል ነው፡፡ለአድሃሪዎች በዚህ አካባቢ መጠናከር ዋነኛ ምክንያቶች፣በኤርትራ ክፍለ አገር ከ15 ዓመት በላይ የታጠቀ ትግል ያካሄዱ፣በተለይ እንቅስቃሴያቸው ፀረ አብዮታዊ ከሆነበት ጊዜ ወዲህ ከውጭ አድሃሪ ሃይሎች በሚያገኙት እርዳታ የተጠናከሩ የኤርትራ አድሃሪ ድርጅቶች መኖር፣የሱዳን ለኤርትራ አድሃሪዎችና ለሌሎቹም የኢትዮጵያ መሳፍንት የፀረ አብዮት ትግል ጀርባ ደጀን መሆንና በሰሜን ኢትዮጵያ ያለው ቢሮክራሲ ከእነሱ ጋር የቆመና በእንጭጩ እንዳይቀጩ መከታ መሆን ናቸው፡፡ለዚህ አካባቢ



ሰፊው ሕዝብ በንቃትና በድርጅት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ ዋነኛው ምክንያት ድሃውን አርሶአደርና ሌሎችንም ከአብዮቱ ወገን ሊቆሙ የሚችሉ ሃይሎች ስለ አብዮቱ ምንነት በማስረዳት፣ኢዲዩን፣ኢህአፓንና አድሃሪ ተገንጣይ ቡድኖችን እንዲሁም አድሃሪውን ቢሮክራሲ በማጋለጥ የተደረገ አጥጋቢ የፖለቲካ ትግል አለመኖር ነው፡፡

ባሁኑ ወቅት በጎንደር ክፍለ አገር ተጠናክሮ ያለው የኢዲዩ ሠራዊት በመጠኑም በመደበኛ መለዮ ለባሹ የአካባቢውን ሰፊ ሕዝብ ለማንቃት ለማደራጀትና እራሱን የአካባቢውን ፀረ አብዮት ለመቋቋም እንዲችል ለማብቃት ገና ብዙ ትግል መደረግ ይኖርበታል፡፡

በትግራይ ክፍለ አገር ያሉ ፀረ ሕዝብ ድርጅቶች እንዳሰቡት ሰፊውን የትግራይ ገበሬ አወናብደው ከጎናቸው ለማሰለፍ ካለመቻላቸውም በላይ በእርስ በርስ ሽኩቻና ከመለዮ ለባሹና ከአርሶአደሩ በየጊዜው በደረሰባቸው ጥቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከሙ መጥተዋል፡፡ ነገር ግን የኤርትራ አድሃሪ ድርጅቶች ጦርነቱን ወደ ትግራይ ክፍለ አገርም ጭምር ለማዛመት በሚያደርጉት ጥረት ገፍተውበታል፡፡ስለሆነም፣የትግራይ ሰፊ ሕዝብ በዚህ አካባቢ አድሃሪዎች የሚያካሄዱትን ፀረ አብዮት ዘመቻ ለመቋቋም እንዲችል ገና የከረረ ትግል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በሰሜን ኢትዮጵያ ያለው ፀረ አብዮት የጀርባ አጥንት የኤርትራ አድሃሪ ድርጅቶች ናቸው፡፡በነዚህ ድርጅቶች የሚመራው የኤርትራ እንቅስቃሴ በወቅቱ የነበረው ተራማጅ ይዘት ተሟጦ አልቆ ሙሉ ለሙሉ ፀረ አብዮታዊ ከሆነ ወዲህ የኢትዮጵያ አድሃሪዎች በሙሉ ለአብዮቱ ቀልበሳ ከቢሮክራሲው ቀጥሎ ተስፋ የጣሉበት እንቅስቃሴ ሆኗል፡፡ኢምፔሪያሊዝምና የጉረቤት ጠላቶች የኢትዮጵያን አብዮት የመቀልበሻና አንድነቷን የመፈታተኛ መሳሪያቸው አድርገዋታል፡፡ የኤርትራ አድሃሪ ድርጅቶችም ባንድ ወገን የኢትዮጵያን አብዮት ሃይል ለማዳከም የሚያደርጉትን አድሃሪ የታጠቀ ትግል እያፋፋሙ ሲሆን፣በሁለተኛ ደረጃም እንደ ኢዲዩና ኢህአፓ የመሰሉ ፀረ ሕዝብ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ ከፍተኛ ወታደራዊና ቁሳቁሳዊ ድጋፍ እየሰጡ ነው፡፡

በኤርትራ ያለውን ሁኔታ አሳሳቢ የሚያደርገው የነዚህ አድሃሪ ድርጅቶች መጠናከርና አድሃሪ አመጻቸውን ማስፋፋት ብቻ ሳይሆን የኤርትራ ሰፊ ሕዝብ የርሱ ነፃነት ከነዚህ አድሃሪ ድርጅቶች ድል ጋር ሳይሆን ከኢትዮጵያ አብዮት ድል መምታት ጋር የተያያዘ መሆኑን እንዲረዳ ስር የሰደደ ቅስቀሳ አለመደረጉ፣ከኤርትራ ተራማጆች ጋር የጠበቀ ህብረትን ፈጥሮ ከእነርሱ ጋር በመተባበር የኤርትራን አድሃሪዎች ለማጋለጥና ለመታገል በቂ ጥረት አለመደረጉ ነው፡፡ምንም እንኳን በግንቦት 8/68 የፖሊሲ ውሳኔ ለነዚህ ተግባሮች ጥርጊያ መንገዱ ለመከፈት ቢችልም፣ብዙም ስላልተገፋበትና ዝርዝር በአመ

ዛኙ ወታደራዊ መፍትሄ ላይ ማዘንበሉ ስለቀጠለ የኤርትራ ገበሬ፣ የኤርትራ ወዛደር ዛሬም ከአድሃሪያቹ ተጽእኖ ተላቆ ከኢትዮጵያ አብዮት ጐን አልተሰለፈም:: የኤርትራን ሰፊ ሕዝብ ያላቀፈ ታክቲካዊ ሆነ ወታደራዊ ትግል የኤርትራን አድሃሪያቹ ለመቋቋምና በመጨረሻም ለመደምሰስ ስለማያበቃ፣ ለኤርትራ ችግር ፖለቲካዊ መፍትሄ ለመስጠት የሚደረገው ጥረት በከፍተኛ ደረጃ መቀጠል ይኖርበታል::

ለማጠቃለል፣ የሰሜን ኢትዮጵያ ችግር የፀረ አብዮት ሃይሎች መጠናከር ብቻ ሳይሆን በዚህ አካባቢ ያሉ የአብዮቱ ወገኖች አለመጠናከርም ጭምር ነው:: ስለሆነም፣ በሰሜን ኢትዮጵያ አድሃሪያችን ለማዳከም የሚደረገው ወታደራዊ ትግል በዚህ አካባቢ ያሉትን የአብዮቱን ወገኖች ለማንቃት፣ ለማደራጀትና ለማጠናከር ከሚደረግ ፖለቲካዊ ትግል ጋር ተጣምሮ ካልተካሄደ፣ ይህ አካባቢ የኢትዮጵያን አብዮትና አንድነት ለሚፈታተኑ የውስጥና የውጭ ጠላቶች አመቺ እንደሆነ ይቆያል፣ ከዚህ አካባቢ በአብዮታችንና በአገራችን ላይ የሚመነጨው አደጋ እየጨመረ ይሄዳል::

## ለ/ የደቡብ ኢትዮጵያ ሁኔታ

በአጠቃላይ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ ክፍላተ አገር ከየካቲት እንቅስቃሴና በተለይም ከመሬት አዋጁ ጀምሮ ለአብዮቱ ምቹ እንደነበሩና የዚህ አካባቢ አርሶአደሮች ከአድሃሪው ቢሮክራሲና ከመሬት ከበርቴዎች ጋር ባካሄዱት የከረረ ትግል፣ ተራማጅ ዘማቾች ሰፊውን አርሶአደር በማንቃትና በማደራጀት ረገድ ያደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ተደምረው ለአብዮቱ ሰፈር የተወሰነ ጥንካሬ ሰጥተው እንደነበር የሚታወስ ነው:: ነገር ግን የዚህ አካባቢ የአብዮት ሃይሎች ጥንካሬ በየወረዳቸው ያለውን አድሃሪ ጭጭ ያሰኘ ጥንካሬ እንጂ በአገር አቀፍ ደረጃ የተነሳውን ፀረ አብዮት ለመቋቋም ወይንም ተጠናክሮ የመጣን ጠላት ለመመከት የሚያስችላቸው ጥንካሬ አልነበረም:: የአካባቢው ተራማጅ ሃይሎችና አርሶአደሮች ይህንኑ በመረዳታቸው፣ በይበልጥ ተደራጅተውና ታጥቀው የበለጠ የተጠናከረን ጠላት ለመቋቋም እንዲችሉ፣ በመደራጀት ጥረታቸው እንቅፋት የሚሆኑባቸው አንዳንድ አድሃሪ ቢሮክራቶች እንዲነሱላቸው፣ የትጥቅ ጥያቄያቸው በአፋጣኝ መልስ እንዲያገኝ ከፍተኛ ትግሎች አካሂደዋል:: የአካባቢውን ሕዝብ ደካማ ጎንና ለዚህ ደካማ ጎን መሻል የቢሮክራሲውን እንቅፋትነት የተረዳቸው ሶማሊያና ሌሎችም አድሃሪያች፣ በታጠቁ ሰርጎ ገቦች የሚያካሂዱትን የትጥቅ አመጽ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያባባሱ መጥተው፣ ዛሬ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ ክፍላተ አገር ያለው የሃይል ሚዛን፣ ቀደም ሲል እንደነበረው ሳይሆን፣ ለፀረ አብዮት ሃይሎች እንዲያደላ እያደረጉት ነው:: መላ ዋለባሹ ከውስጥ አድሃሪ ሃይሎች ጋር በመተባበር የሚያደርጉትን ጥቃት ለብቻ መቋቋም ስለማይችልና አርሶ አደሩ ባዶ እጁን በመሆኑ ከመደበኛው መለዮ ለባሽ ጎን ለመሰለፍ ስላልቻለ፣ በነዚህ ቦታዎች የፀረ አብዮት ትግል ከመፋፋሙም ፀረ አብዮታዊ ሃይሎች አንዳንድ



አውራጃዎችን በቁጥጥራቸው ስር እስከማድረግ ደርሰዋል:: አድሃሪው ቢሮክራሲ፣ ለምሳሌ ያህል በሐረርጌ፣ በገቢር ሁኔታውን ለሰርጎገቦችና ለአካባቢው አድሃሪያች ከማመቻቸቱም አልፎ ፊት ለፊት በአብዮቱ ወገኖች ላይ ዘመቻውን ቀጥሏል::

## ሐ/ የመሃል አገር ሁኔታ

በዚህ ክፍል ባጭሩ የምንመለከተው በተለይ የአዲስ አበባንና የአካባቢውን ሁኔታ ነው:: የአድሃሪው ቢሮክራሲ እምብርት፣ የፊውዳሉ መደብ ርዝራዦች፣ ቀኙ ክንፍ ንዑስ ከበርቴና የሲአይኤ መገልገያ የሆኑ ድርጅቶች የመሸጉት አዲስ አበባ ነው:: የአድሃሪያች የትጥቅ አመጽ የተፋፋመው በዳር ክፍላተአገር ቢሆንም በተለይ ማእከላዊውን መንግሥት ለመገልበጥና ስልጣን ሙሉ ለሙሉ ለመጨበጥ ዋናው ስራ የሚጠነጠነው አዲስ አበባ ነው::

ባንፃሩ፣ አያሌ የነቁ ሠርቶአደሮች፣ ተራማጅ ሃይሎችም በአዲስ አበባ ውስጥ ይገኛሉ:: ትልቁ ቁጥርም ያለው መሃል በፋሪም አለ:: ባንዱ ቃል፣ አዲስ አበባ የፀረ አብዮት ቀንደኞችና የአብዮቱ መሪ ሃይሎች የሚገኙባት ከተማ ነች:: በነዚህ ተፃራሪ ሃይሎች መሃል በተደረገው ከፍተኛ ትንንቅ እስካሁንም አንደኛውም አሸናፊነት አላገኘም::

በተለይ ሠርቶአደሩ ከወዝገበር ወደጥራት ተሸጋገሮ፣ ጠላቶቹን ለመደምሰስ ይበልጥ ቁርጠኛ መሆኑ፣ ለዚህም የሚያገለግሉት ድርጅቶችን ከፀረ አብዮተኞች ማጽዳቱና የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም መቻሉ፣ እነዚህ ሁሉ ለአብዮቱ ወገኖች በተሻለ ሁኔታ ላይ መገኘት ምልክቶች ናቸው:: ዳሩ ግን፣ ይህ የአብዮቱ ወገኖች መጠናከር ጠላቶቻቸውን ለመከርከም እንጂ ለመርገጥ አለበቃቸውም:: አሁን ባለው ሁኔታ፣ የሃይሉ ሚዛን ተመልሶ ለአድሃሪያች እያደላ፣ ወደአጥቂነት ለመሸጋገር ፋታ አግኝቶ የነበረው አብዮት ተመልሶ ወደ ተከላካይነት ተወርውሯል:: አንገት መደፋት ጀምረው የነበሩት አድሃሪያችና ቀጥር ነፍስ ገዳዮች መልሰው መንሰራራት ይዘዋል:: አድሃሪው ቢሮክራሲ ከጥር 26 ድንጋጤው አገግሟል:: እንደዚህ በመሆኑም፣ እስከዛሬም ድረስ አያሌ የቀበሌ መሪዎችና ተራማጆች በገላገል ፋሺስቶች ጥይት እየረገፉ ናቸው:: የገላገል ፋሺስቶች ጥይት አንገቧቸው በሰበብ አስባብ እየተያዙ የሚታሰሩ የቀበሌ ተራማጆች ቁጥር በርክቷል:: ባንፃሩ "መረጃ አልተገኘባቸውም" ወይንም "ሄዱና ገለሄ አድርገው ታርመዋል" በሚሉ ከእውነት የራቁ ሰበቦች የሚፈቱ ወይንም የማይያዙ ቀጥር ነፍስ ገዳዮች ቁጥርም እየጨመረ ነው:: አድሃሪው ቢሮክራሲ ፊት "ኢሀአፓን አትንኩ" በሚል ገለጻ አጅ የሚሰራውን ደባ ዛሬ ደግሞ "ኢሀአፓ ይውደም" በሚል ሽፋን ስር ቀጥሎበታል::

የሰፊውን ሕዝብ ወገኖች የመለከትን እንደሆነ፣ በአብዮቱ ላይ ያላቸው

እምነትና በፀረ አብዮት ላይ ያላቸው ጥላቻ ዉምር ይገኛል፡፡በአዲስ አበባ ውስጥ ብቻ እስከሁን ከመቶ በላይ የቀበሌ ማህበር መሪዎች ሲገደሉ የቀሩት ተመራጮች የቀበሌ ማህበር ጽሕፈት ቤታቸውን ከመዝጋት ይልቅ የወደቁትን ጓደቻቸውን የትግል አርማ ይዘው በትግል መግፋታቸው ለዚህ በቂ ማረጋገጫ ነው፡፡ ሆኖም ገን፣በአብዮቱ ላይ ያላቸውን የጠመረ እምነት አብዮታቸውን ወደፊት በማራመድ እንዳይገለጹት፣በጠላቶቻቸው ላይ የጠመረውን ጥላቻ ጠላቶቻቸውን በማጥቃት እንዳይገለጹት አንደኛ የተጥቀ ጥያቄያቸው ተገቢ መፍትሄ አላገኘም፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው የሁለት ጊዜ አሰሳ የመጀመሪያው አሰሳ በተካሄደበት ወቅት የከተማው ነቀ ወዛደሮች ከመለዮለባሹ ጋር ተባብረው ከአዩሃሪ ጋር እየተዋደቁ ያስፈቱት ትጥቅ መንግሥት ግምጃ ቤት ገብቶ ቀጭ ብሏል፡፡ የሁለተኛው ጊዜ አሰሳ የተዝረከረከ መልክ ስለነበረው አጥጋቢ ውጤት አላስገኘም፡፡ሁለተኛም፣በአድሃሪው ቢሮክራሲ አንቀፋትነት ህዝባዊና ነፃ እርምጃዎች ታፍነዋል፡፡ይህ የአድሃሪው ቢሮክራሲ አንቀፋትነት ተጋልጦ እንዳይወገድ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች አሁንም አልተለቀቁም፡፡ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትም ከሰፊው ሕዝብ ይልቅ በቢሮክራሲው ላይ የመተማመን መስመር ይዟል፡፡ እንግዲህ፣ይህ ሁሉ የሚያሳየን ባንድ በኩል በአዲስ አበባም ፀረ አብዮት

የተጠናከረ የአብዮቱ ወገኖች በሚገባ ያልተጠናከሩ መሆናቸውን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣በአብዮታችን ላይ የሚያንዣብበው የቀለበሳ አደጋ የአድሃሪያች የተጥቀ አመጽ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ላይ ብቻ አይደንን መተከለ ከመሃል አብዮቱን ለመቀልበስ ለሚዘጋጀው ፀረ አብዮት አድል ለመስጠት ነው፡፡ይህ ሁኔታ እንዲቀየር፣የአብዮቱ ወገን መጠናከር በተለይም እንዲታጠቅ መደረግ አለበት፡፡ የአብዮቱ ወገኖች በጠላቶቻቸው ላይ የማጥቃት እርምጃቸውን እንዲቀጥሉ ማገዝ፣በአድሃሪው ቢሮክራሲ ላይ ዘመቻ ማፋፋምና ለአድሃሪው ቢሮክራሲ ማፈግፈግ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥረት የዲሞክራቲክ መብቶች ለጭቁኖች መገኘት ይኖርበታል፡፡

መ/ <u>የአካባቢው ሁኔታ</u>

በኢትዮጵያ አብዮትና አንድነት ላይ ከውጭ የመጣውን አደጋ ለመረዳት ከነሱዳን ከነሱማሌ አልፍ በዚህ ክፍለ ዓለም ካለው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዓላማ አንጻር መመልከት ያስፈልጋል፡፡በዚህ ክፍለ ዓለም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከእጁ ወጥተው የነበሩ አገሮችን መልሶ እያገኘ ነው፡፡እነገብፅ፣እነሱዳን፣በቀርቡ በግልጽ የሚታየውንም የሱማሌን ሁኔታ መመልከት ነው፡፡በአንፃሩ ሶቪየት ህብረት ከነዚህ አገሮች ጋር የነበራት ጥብቅ ግንኙነት ሻከሯል፡፡እንግዲህ፣አካባቢያችንን ስንመለከት፣የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከእጁ የወጡትን አገሮች እያስመለሰ ሲሆን፣እጁ የነበረቸው ኢትዮጵያ ደግሞ እያፈተለከቸበት ነው፡፡ስለሆነም፣የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የኢትዮጵያ አብዮት



ገቡን እንዳይመታ ተለቀ ጥቀም ስላለው ከውጭ አብዮቱን ከበው የሚያሰጡን ቁለት የጐረቤት አድሃሪዎችን እያስተባበረ ነው፡፡በሲአይኤ አማካይነት አድሃሪው ቢሮክራሲ ውስጥ ውጭ ያሉ ሃይሎችን እያጠናከረ ነው፡፡እንደሱዳንና ግብፅ የመሳሰሉት አድሃሪ መንግሥታትም የኤርትራን አድሃሪዎች በተለያዩ መንገዶች በገፍ እየረዱ ናቸው፡፡

ሱማሌ፣የዚህ የአጠቃላይ ፀረ አብዮት ከበባ አካል በመሆኗ ለፀረ አብዮት ሃይሎች ከምትሰጠው እርዳታ በላይ የአብዮቱ ወገኖች በተለያዩ ቦታዎች መወጠር የርሷን ጁሹቷን የመያዝና ከኢትዮጵያ ግዛትም አጋዴንን የመያዝ እድል ከፍ ስለሚያደርግላት የሰለጠኑ ሰርጎገቦችን እስከ አረሲ ድረስ በመላክና በዚህ አካባቢ የሚገኙትን የውስጥ አድሃሪዎች በማስታጠቅ የአብዮቱን ሰፈር ለማዳከምና ፋታ ለማሳጧት ከፍኛ እየተጣጣረች ነው፡፡በተለይ ከቅርብ ጊዜ በፊት ጀምራ ግልጽ የሆነ ጦርነት በማካሄድ ላይ ተገኛለች፡፡

እንግዲህ አካባቢያችንን ለአብዮታችን ምቹ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማናጋትና በመጨረሻም አብዮቱን ለመቀልበስ በሚፈለጉ ለዚህም ከፍተኛ ትግል በማድረግ ላይ ባሉ ጠላቶች ተከበናል፡፡ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን የሚያዝል ጠላት ከነዚህ የጐረቤት ጠላቶች ጉን ቆሟል፡፡ስለሆነም፣ይህ የጠላት ከበባ ባጭር ጊዜ ወታደራዊ ትግል የምንሰብረው ከበባ አይደለም፡፡ ሰፊው ሕዝብ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶና ነቅቶ ሲጠበቅ፣በጥንቃቄና በብልሃት የሚመራ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ትግል የነዚህን የጐረቤት አገር ጭቁን ሕዝቦች፣በዓለም አቀፍ ደረጃም ለሃቀኛ ብሔራዊ ነፃነት፣ለእኩልነትና ለሰላም የቆሙ ሃይሎች ሁሉ ሳይከፋፈሉ ከኛ ጉን እንዲቆሙ ስናደርግ ብቻ የምናከሽፈው ከበባ ነው፡፡

እስከሁን ካየነው የኢትዮጵያ አብዮትና የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች አንድነት ጠላቶች በውስጥም በውጭም ተጠናክረው ከፍተኛ የቀለበሳ ትግል እያካሄዱ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ይህንን የውስጥና የውጭ ጠላቶች የቀለበሳ ትግል ለማክሸፍ ካሁኑ በበለጠ መንቃት፣መደራጀትና በተለይም መታጠቅ፣ካሁኑ በበለጠ ለረጅም ወራራ ትግል ባፋጣኝ መዘጋጀት፣ካሁኑ በበለጠ ጭቁኖች ከዳር እስከዳር መቀስቀስና መንቀሳቀስ እንዳለባቸው እንረዳለን፡፡

ተራማጆች አድሃሪዎችን ገሸሽ ስላደረግን አሸነፍን ብለን የምንፈነድቀውን ያህል፣ተጠናከሩ ብለንም ተከፋ አንቆርጥም፡፡ የመደቦች ትግል በከረረ የረጅም ጊዜ ትግል በጭቁኖች አሸናፊነት ከግቡ ይደርሳል እንጂ በአቋራጭ የሚገኝ ድል የለም፡፡ደግሞም ጭቁኖችና ወዳጆች በሚያደርጉት ጦርነት ሁሉም ለተቃራኒ አላማዎች ተሰባስቦ ዝግጅት አርገው በሞትና በሽረት ትግል አሸናፊው

ይታወቃል እንጂ የፍርሬ ተሸናፊነት ወይም አሸናፊነት የለበትም፡፡ስለሆነም የአድሃሪያቸ መጠናከር የሰፊውን ሕዝብ ነፃ መውጣት ለማስቀረት ወይም ለማዘግየት የጠላት ሰፈር ማድረግ ያለበትን ነገር በለማያመለከት አንገረምበትም፡፡ ከዚህ የምንወስደው መደምደሚያ ሰፊው ሕዝብ ከጠላቶቹ ይበልጥ ነቅቶ፣ከጠላቶቹ ይበልጥ ተደራጅቶና ተባብሮ በወሳኙ ግጥሚያ አሸናፊ ለመሆን መዘጋጀት እንዳለበት ብቻ ነው፡፡ የአብዮቱ ሃይሎች ሁሉ ይህንን ተረድተው ሌት ተቀን ለሰፊው ሕዝብ ሰፈር መጠናከርና ለመራራው ትግል ይበልጥ መዘጋጀት ከታገሉ የአሁኑ የውስጥና የዉጭ ጠላቶች የቀለበጣ ትግል ከሽፎ ብሄራዊ ነፃነቷን ያስከበረች፣ኩሩ፣ታጋይና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንደምትገነባ ምንም ጥርጥር የለዉም፡፡

<u>ስለ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ</u>

በአጠቃላይ ደርጉ የንዑስ ከበርቴ መንግሥት እንደሆነ፣እረማመዱም የዚሁ መደብ ወላዋይነት እንደሚያንፀባርቅ፣እንደገናም ደርጉ በግራና በቀኝ ክንፍ የተከፈለና በሁለቱ ክንፎች መሃል በሚደረገው ትግል በየወቅቱ የግራው ወይም የቀኙ ክንፍ ማየለ የአብዮት ወይንም የፀረ አብዮት አዝማሚያን መጠናከር ከሚወስኑት ጉዳዮች አንዱ መሆኑ ተደንግጎ ተነግሯል፡፡እንደዚሁም ደግሞ፣ደርጉ በአብዮትና በፀረ አብዮት መሃል በለሚዋልል የህዝብ ወገኖችም የሕዝብ ጠላቶችም ተጽእኖ እንዳለበት የታወቀ ነው፡፡

በአጠቃላይ ደርጉ ከፊውዳሊዝምና ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር ተፃራሪ ቅራኔ ውስጥ ከወደቀ ቆይቷል፡፡በደርጉና በነዚህ ቀንደኛ ጠላቶች መሃል ይህ ቅራኔ መኖሩና ደርጉ በተጨባጭ የወሰዳቸው ተራማጅ እርምጃዎች ከሰፊው ሕዝብ ወገን አስደምረውታል፡፡ቢሮክራሲውን በሚመለከተው በኩል ግን፣እርግጥ በደርጉና በቢሮክራሲው መሃል የተወሰነ ቅራኔ ቢኖርም፣በዚህ አድሃሪ ተቋም ስለሚጠቀም ባጠቃላይ በቢሮክራሲው ጥያቄ ላይና በተለይም በሰፊው ሕዝብና በቢሮክራሲው መሃል በሚፈጠሩ ግጭቶች ፍጹም ወላዋይ ነው፡፡

እስካሁን ድረስ ከሞላ ጎደል፣በአንዳንድ ወቅቶች በስተቀር፣ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከሰፊው ሕዝብ ጎን ቆሟል፡፡በአንዳንድ ወላዋይና አድሃሪ እርምጃዎች የአብዮቱን እድገት ቢጎትትም ከሞላ ጎደል በአብዛኛው ለአብዮቱ እርምጃ የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ከእንግዲህስ የሚለውን ጥያቄ በሚመለከተው ተራማጆችና ሰፊው ሕዝብ የሚከተሉትን ሁለት ዋነኛ ነጥቦች መገንዘብ አለባቸው፡፡



1. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከሕዝብ ወገን መቆም አለመቆም፣ ከየተጨባጭ ሁኔታው አንፃር እየተመረመረ የሚታይ እንጂ አስቀድሞ የሚወሰን ጉዳይ አይደለም፡፡ የደርጉ የሕዝብ ወዳጅ ሆኖ መቆየት ወይንም አለመቆየት በአብዮቱ ወሳኝ ጥያቄዎች ላይ በሚወስዳቸው እርምጃዎች በተጨባጭ የትኛውን ወገን እንደጠቀመና የትኛውን ወገን እንደጎዳ እየተመረመረ የሚመለስ ጥያቄ ነው፡፡ለምሳሌ በዛሬው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፣ደርግ በቢሮክራሲው ጉዳይ፣በዴሞክራሲያዊ መብቶች ጉዳይ የሚወስደው አቋም ወይ ከሕዝቡ ጎን ወይ ባጠቃላይ ከቀለበሸ ሃይሎች ጎን ያሰልፈዋል፡፡እርግጥ፣ ተራማጅ ሃሎችና የነቁ ሰርቶአደሮች ደርጉ በወሳኙ የአብዮቱ ጥያቄ ላይ የኢትዮጵያን ጭቁኖች ትግል የሚያግዙ እርምጃ እንዲወስድ መታገል አለባቸው፡፡ ባጠቃላይ በደርጉ ወላዋይነትና በቢሮክራሲው ላይ ለመተማመን ባደረገው ምርጫ የደርግ እርምጃዎች ለአብዮቱ ግስጋሴ የሚጎዱ እንጂ የማይጠቅሙ ከሆኑ፣በደርጉና በሰፊው ሕዝብ መሃል ያለው ቅራኔ ይከራል፡፡ይህም ሰፊው ሕዝብ ጠላቶችን ለመደምሰስ በሚያደርገው ትግል ደርጉን ተለቅ እንቅፋት ወደመሆን ይቀይረዋል፡፡

2. ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን ፕሮግራም ቢቀበልም፣እስከመጨረሻው ግብ ድረስ ሊመራ አይችልም፡፡ የብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ዋና ይዘቶች በርሱ አገዛዝ ስር ሥራ ላይ ሊውሉ አይችሉም፡፡ይህን ሊያደርግ የሚችለው የወዝአደሩ መደብ ብቻ ነው፡፡ይህንንም የምንለው በአጠቃላይ ከንዑስ ከበርቴነቱ ከወላዋይነቱ አንፃር ብቻ ተመልክተነው ሳይሆን፣በውስጡ የለየላቸው አድሃሪያቸ ጭምር የሚገኙበትና በተግማማው አድሃሪ ቢሮክራሲ የሚገለገል መንግሥት በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ስለሆነም፣ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን የመምራት ታሪካዊ ሃላፊነት ያለበት በወዛደሩ መደብ ፓርቲ የሚመራ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ተቋቁሞ የዛሬውን የኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል እስካልመራ ድረስ፣የዚህ አብዮት እድል ከደርጉ ጋር እስከተያያዘ ድረስ አብዮታችን ምንም አስተማማኝ አመራር አይኖረውም፡፡እንደዚሁም፣በዚሁም ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር መሪነት በዛሬው አድሃሪ ቢሮክራሲ ሬሳ ላይና በደርጉ ቦታ በወዛደሩ መሪነት፣በወዝአደር — አርሶአደር ሕብረት ላይ የተመረኮዘ ሌሎች ፀረ ቡበት ሃይሎችን ያቀፈ ሃቀኛ ሕዝባዊ መንግሥት እስካልተመሰረተ ድረስ የብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ዋና ዋና ይዘቶች በሚገባ ሥራ ላይ ሊውሉ አይችሉም፡፡ስለዚህ፣ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ከሞላ ጎደል ተራማጅ እርምጃዎችን ቢወስድም፣የወዝአደሩን ፓርቲና በዚሁም ፓርቲ መሪነት ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩን ለመመስረት፣የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ለመንግሥት ስልጣን ንጥቂያ ለማብቃት የሚደረገው ትግል እጅግ መፋፋም አለበት፡፡

## ስለ ቢሮክራሲ

ከሃይለ ስላሴ የተወረሰው የተንማማ ፀረ ሕዝብ ቢሮክራሲ እስካሁን ድረስ በሚገባ የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ በትር ያላረፈበት፤እንዲያውም የሰፊውን ሕዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ አፍኖ የያዘ መዋቅር መሆኑን የማይታበል ሃቅ ነው::ይህ ቢሮክራሲ በመደብ ይዘቱ ፍጹም አድሃሪ ከመሆኑም በላይ ለማንኛውም ፀረ አብዮታዊ ቡድንና መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የሰጠ ነው::የፀረ አብዮት ሤራዎችም በተካሄለት ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሰረት ለሚቻለው ፋሺስታዊ ስርዓት ተሸካሚ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው::

ይህ አድሃሪ ቢሮክራሲ በዚህ በፊት የደርግን ወዳጅ በመምሰል በከፍተኛ የአመራር ቦታዎች ሰርጎ ለመግባትና ደርግን ለመከበብ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው::በአንድ በኩል ደርግንና ተራማጆችን በማቃቃር በሌላ በኩል ደግሞ የደርግ አገልጋይ በመምሰል እየሰራለት ለፀረ አብዮት ሤራዎች አመቺ ሁኔታ በመፍጠር ላይ ይገኛል::

ስለሆነም ከቢሮክራሲው በኩል ለመጡ የሚችሉት ፀረ አብዮታዊ ሙከራዎችን ለማቋቋምና ለአብዮቱ እድገት መንገድ ለመጥረግ በዚሁ ፀረ አብዮታዊና አድሃሪ ቢሮክራሲ ላይ የማያወላውል አብዮታዊ እርምጃ መውሰዱ ያስፈልጋል:: ቢሮክራሲውን ለመደምሰስ በሚደረገው አብዮታዊና ታሪካዊ ጥረት በመጀመሪያ ደረጃ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰዱ ይቻላል::

ሀ/ ቁልፍ በሆኑ ቦታዎች ላይ የሚገኙትን አድሃሪያንን አንስቶ በሃቀኛ ተራማጆች፣ሃገር ወዳዶችና ዲሞክራቶች መተካት
ለ/ የቢሮክራሲውን ጠቅላላ የአሠራር ዘዴ የሚያሻሽል መዋቅር መቀየስ
ጠ/ ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲያብቡ ከፍተኛ ትግል ተደርጎ፣በባቢያውም የአስተዳደር ተግባሩን ደረጃ በደረጃ እንዲረከቡ ማድረግ::

ቢሮክራሲው ቀንደኛ የሕዝብ ጠላት ሆኖ ባለ፣ከቀርብ ጊዜ ወዲህ ለስልጣን የቋመጡ አድሃሪ ባለስልጣኖችና የቢሮክራሲው አቀንቃኞች የተራማጅ ካባ ተከናንበው "ቢሮክራሲው ተራማጅ ነው"፣ "ለአብዮቱ ጠቅሟል"፣ "ቢሮክራሲው ይውደም የሚሉ ገራ ቀደሞች ናቸው" ወዘተ የሚል ፍጹም ፀረ ሳይንሳዊ የሆነ የቢሮክራሲውን ምንነት ያልተረዳ ፀረ አብዮታዊ ፕሮፓጋንዳ መንዛት እንደጀመሩ የታወቀ ነው::የኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆች ይህን ፀረ አብዮታዊ ፕሮፓጋንዳ በማጋለጥ ቢሮክራሲው፣እንዲመታ፣የተራማጅ ደርግ አባሎችና የሰፊው ሕዝብ አንድነት እንዲጠነክር ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው::



## ስለዲሞክራሲያዊ መብቶች

የየካቲት 66ቱ እንቅስቃሴ ይዞ ከተነሳቸው አብዮታዊ ጥያቄዎች አንዱ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ነው::ከዚያም ጊዜ ወዲህ ሰፊው ሕዝብ እንዱ የተወሰኑ መብቶችን እየነጠቀ ሲጠቀምባቸው፣አንዳንዴም እየተነጠቀ ሲያፈገፍግ እስካሁን መጥቷል::ዛሬ በእጁ የሚገኙ፣እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ የሚገለገለባቸው ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ተቀዳጅቷል::ነገር ግን፣የሰፊው ሕዝብ ትግል የደረሰበትን የእድገት ደረጃና ከዚህ ደረጃ ወደሚቀጥለው ለማለፍ ማድረግ ካለበት አፋጣኝ ዝግጅቶች አንፃር በእጁ ካሉት መጠነኛ መብቶች አልፎ ሙሉ ለሙሉ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማግኘት አለበት::ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ስላልተለቀቁለት በተቀዳጃቸው መብቶች ሙሉ ለሙሉ መጠቀም አልቻለም:: የአድሃሪውን ቢሮክራሲ አሻጥር አጋልጦ የብዙሃኑን ሕዝባዊ ድርጅቶችን ለማጠንከር እንቅፋት በርክቶበታል::ተራማጅ ሃይሎች ሰፊውን ሕዝብ በፖለቲካ እምነቱ አደራጅተው የወዝአደሩን ፓርቲና ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩን ባፋጣኝ ከማቋቋም እየተጓተቱ ነው::ሰፊው ሕዝብ በአብዮቱና በእናት አገሩ ላይ የውስጥና የውጭ ጠላቶች የሚተበትቡትን ሤራ በሚገባ ተረድቶ ይህንን ሤራ ለመበጣጠስ ተገቢ ተሳትፎውን ለማድረግ ታውኳል::ስለሆነም፣የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጉዳይ የአብዮቱ ወሳኝ ጥያቄ እየሆነ ነው::የሰፊዉ ሕዝብ በይበልጥና ባፋጣኝ መንቃት መደራጀትና መታጠቅ ከነዚህ መብቶች መለቀቅና ለነዚህ መብቶች መለቀቅ ከሚደረገው ትግል ጋር በጥብቅ የተያያዘ ሆኗል::

የዲሞክራሲያዊ መብቶችን መለቀቅ አጣዳፊ የሚያደርጉት፣

ሀ. ለወዝአደሩ መደብ ፓርቲና ለሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩ መፈጠር እጅግ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል::በፖለቲካ እምነት አንፃር የመደራጀት መብት ለጭቁኖች ስላልተለቀቀ ተራማጅ ድርጅቶች የማንቃትና የማደራጀት ተግባራቸውን እንደአድሃሪያኖች ሁሉ በስውር እንዲያከናውኑ ተገደዋል::ይህም የሰፊውን ሕዝብ በፖለቲካ ድርጅት ስር መደራጀት ጎትቷል::ለጭቁኖች የመደራጀት መብት በይፋ ቢለቀቅ ግን የመቀስቀስና የማደራጀቱ ተግባር ይፋጠናል::ከዚሁም በላይ፣ለሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርና ለወዝአደር መደብ ፓርቲ መፈጠር መሠረት የሚሆኑትን የተራማጆች ሕብረት ለመፍጠር ተራማጆች እየጣሩ ናቸው::ይህ ጥረት የበለጠ ፍሬ የሚሰጠው፣አሉባልታና ሀሜት ተወግዶ ሃቀኛ ተራማጆችና ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የበለጠ የሚቀራረቡት፣የበር ጉገብ አድሃሪያዎች ከፋፋይ ሙከራዎች የሚወገዱት፣እነዚህ ድርጅቶች በሰፊዉ ሕዝብ ውስጥ በይፋ ለመታገል ሲችሉና በዚህም የይፋ ትግል ውስጥ በይበልጥ እርስ በርስና ከሰፊው ሕዝብ ጋር እየተሳሰሩ በዲሞክራሲያዊ የሁለት መስመር ትግል በዋነኛ የአብዮቱ ጥያቄዎች ላይ ከመግባባይ አቋም ላይ ሲደርሱ ነው::ስለሆነም፣የሰፊው ሕዝብ በይበልጥ

መንቃቱ፣በተለይም በተራማጁ የፖለቲካ ድርጅቶች አከባቢ በደበለጥ መደራጀት እንዲቻልና እንዲፋጠን ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ባስቸኳይ መለቀቅ አለባቸዉ::

ለ. ለአድሃሪው ቢሮክራሲ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አሻጥሮች መጋለጥና መክሸፍ፣ ለአዲስ ሕዝባዊ ሃይሎች በደበለጥ መጠናከር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል::ደርግ ወደደ ጠላ ከሃይለ ስላሴ በተወረሰው ቢሮክራሲ ይጠቀማል::ነገር ግን ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ያወጣቸው ተራማጅ መመሪያዎችን፣ከነዚህም ጋር ተያይዘው ለሰፊው ሕዝብ የተለቀቁ መብቶችን የሚያንፀባርቁ አዋጆችን ቢሮክራሲው ለማደናቀፍ እንጂ ሥራ ላይ ለማዋል አይችልም::እነዚህን ድሎች ተመርኩዘው የተፈጠሩ አዲስ ሕዝባዊ ሃይሎች በደበለጥ ተጠናክረው እነዚህን ተራማጅ መመሪያዎች በተግባር ለመተርጐም፣በህግ የተለቀቁላቸውን መብቶች በሚገባ ለመጠቀም ሲታገሉ ቢሮክራሲው ማነቆ ሆኖባቸዋል፣ይሆንባቸዋልም::አሁንም የቢሮክራሲው የስልጣን ድርሻ ከፍተኛ ስለሆነ፣ከአዲሶቹ ሕዝባዊ ሃይሎች ጋር ሲወዳደሩ በስልጣንም በጉልበትም የላቀ ስለሆነ አድሃሪው ቢሮክራሲ ትልቅ ወደኋላ ጎታች ሃይል ሆኗል::ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬውኑ ቢሮክራሲውን ደምስሶ የራሱን ስልጣን በቦታው ማቆም እንደማይችል የታወቀ ነው::ከዚህ ግብ ለመድረስ ግን ዛሬ በዲሞክራሲያዊ መብቶች እየተጠቀመ እራሱን ለማጠናከርና የአድሃሪውን ቢሮክራሲ አሻጥሮች ለማጋለጥና ለመቋቋም መቻል አለበት::ባንፃሩ ደግሞ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ስለመለቀቅ ቢሮክራሲው ስልጣኑን መከታ አድርጎ ሰፊውን ሕዝብ እንዲጨቁን፣በማን አለብኝነት የፖለቲካና የኢኮኖሚ አሻጥር እንዲያፋፍም ጥሩ ሁኔታ ፈጥሮለታል::ስለሆነም፣የዲሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ፣ቢሮክራሲው እንዲያፈገፍግ የሚገደድበትና የሰፊው ሕዝብ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥራል::

ሐ. የዲሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ በውስጥና በውጭ አድሃሪዎች የሚሸረቡትን ሤራዎች በሚገባ እንዲጋለጡ፣ሰፊው ሕዝብ ባጠቃላይ በአብዮቱ ውስጥና በተለይም የአድሃሪዎችን ሴራዎች ለማክሸፍ በሚደረገው ትግል ውስጥ በደበለጥ እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል::እስካሁን ማእከላዊ መንግሥቱን ለመገልበጥ የተደረጉ ፀረ አብዮት ሴራዎች በአጋጣሚ በመንግሥት ክትትል ከሽፈዋል::ሰፊው ሕዝብ ሴራዎቹ ሲከሸፉ ለማውገዝ ወጣ እንጂ፣የደስታ ተካፋይ እንዲሆን ተጋበዘ እንጂ ስለሴራዎቹ ምንነት ተረድቶ እነዚህን ለማክሸፍ የተደረገው ጥረት ተሳታፊ አልነበረም ::ዛሬ በአብዮታችንና በእናት አገራችን ላይ የሚያንዣብበው አደጋ በአጋጣሚ የሚወገድ ወይንም በደርግ ብቻና ያውም በአድሃሪው ቢሮክራሲ አማካይነት የሚደመሰስ አደጋ አይደለም::የሰፊውን ሕዝብ ስለዚህ አደጋ በሚገባ መረዳትና ይህንኑ ለማክሸፍ ከዳር እስከዳር መቀስቀስና መንቀሳቀስ ይጠይቃል::ባንድ ቃል፣



በሰፊው ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ ብቻ የሚወገድ አደጋ ነው::የዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ባስቸኳይ መለቀቅ ሰፊውን ሕዝብ ከዳር እስከዳር ለማንቀሳቀስ በርሱው ሙሉ ተሳትፎ ፀረ አብዮትን ለመደምሰስ መብቃት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል::

መ. ሰፊው ሕዝብ በትግሉ ስለሚያጋጥሙት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በነፃ እንዲወያይ፣መፍትሄያቸውንም ከአብዮቱ መግፋት ጋር አያይዞ እንዲመለከት ያስችለዋል::

ሠ. ሰፊው ሕዝብ አሮጌውን ስርዓት ደምስሶ አዲስ ህይወት ለመገንባት በሚያደርገው ጥረት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ኑሮን ለመለማመድ ያስችለዋል::

እነዚህና ሌሎች ምክንያቶች የዲሞክራሲያዊ መብቶችን መለቀቅ እጅግ አጣዳፊ በማድረጋቸው ሰፊው ሕዝብ ከዳር እስከዳር "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ባስቸኳይ" በሚለው መፈክር ስር ተሰልፎ በመታገል ላይ ነው::ይህ እንደዚህ ሆኖ፣"ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁን ቢለቀቁ የአድሃሪዎች መጠቀሚያ ይሆናሉ" የሚሉና ተመሳሳይ ስንኩል ሰበቦች ከሁለት አቅጣጫዎች መሰንዘር ጀምረዋል::እነዚህም፣ባንድ በኩል በተሳሳቱ መነሻዎች ላይ የተመረኮዙ፣የጠላትን የፖለቲካ ሃይል ከማጋነንና በሰፊው ሕዝብ አብዮታዊነትና ታጋይነት ላይ እምነት ከማጣት የተነሳ በስሜታዊነትና አንዳንዴም በአድርባይነት የተጋረዱ ተራማጆች ሲሆኑ፣በሌላ በኩል ደግሞ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ውስጥ የተሰገሰጉ፣የዲሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ ስልጣናቸውን መከታ በማድረግ የምንሸርበውን ሴራ ያጋልጥብናል ብለው የሰጉ የነቁ አድሃሪዎች ናቸዉ::በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ እንዲለቀቁ ከሚታገሉት የኢትዮጵያ ጭቁኖችና ሃቀኛ ተራማጆች ጋር ያለውን የትግል አንድነት እየገለፀ፣ከላይ የጠቀስነው ስህተተኛ ግምት ያላቸው ተራማጆች አቋማቸውን እንዲያስተካክሉ የሚያደርግ ጥረት እንዲገን በዚህ የአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ላይ ጓዳዊ ውይይት እንዲፋፋም ለሃቀኛ ተራማጆችና ሃቀኛ ዲሞክራቶች ሁሉ ጥሪ ያደርጋል::

ስለ ተራማጆች ሕብረት

የኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆች በሕጋዊና ሕገወጥ ትግል ለኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል::የአብዮቱን አቅጣጫ፣ችግሮችና መፍትሄዎች እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ ለሰፊው ሕዝብ አስጨብጠዋል::ለኢትዮጵያ ሠርቶአደሮች ከነቁ አድሃሪያን ተጽእኖ መላቀቅና በአብዮቱ ሰፈር መሰብሰብ ትልቅ ተጋድሎ አካሂደዋል:: በአገራችን ዛሬ የሚታዩት የፖለቲካ ድሎች

በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ የተደራጁት የኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆች የትግል ፍሬዎች ናቸው።

እነዚህ የተለያዩ ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶች በየፊናቸው ለኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ይህን ያህል አገልግሎት ቢሰጡም እንደተለያዩ ሆነው በአብዮቱ ውስጥ የሚገባቸውን የግንባር ቀደምትነት ቦታ ሊይዙ አይችሉም። ለዚህ የግንባር ቀደምትነት ቦታ ብቁ የሚሆኑት እነዚህ ተራማጅ ድርጅቶች ሕብረት ሲፈጥሩ፣ በዚህ ሕብረት ውስጥ ያሉ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በይበልጥ ተቀራርበው ሲዋሃዱ ብቻ ነው።

በየካቲት ወር 69፣ አምስት ተራማጅ ስወር የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ማለትም መኢሶን፣ ኢጭአት፣ አብዮታዊ ሰደድ፣ የወዝአደር ሊግና ማሌሪድ፣ ይህንን የተራማጆች ሕብረት ለመመስረት በወሰዱት የመጀመሪያ እርምጃ አንድ የጋራ መግለጫና የጋራ መርሃ ግብር ማውጣታቸው ይታወሳል። ይህም ባጠቃላይ ለፀረ ቡስት ሃይሎች ሕብረትና አለፍም ለሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር መገንባት፣ እንደዚሁም ለማርክሲስት ሌኒኒስቶች ውህደትና ለወዝአደሩ ፓርቲ መፈጠር መሠረት ስለሚሆን፣ በአገር ውስጥና ውጭ ያሉ ተራማጅ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በታላቅ ደስታ የሚቀበሉት ነው። ማህበራችን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ለንዲህ አይነት የተራማጆች ሕብረትና ለማርክሲስት ሌኒኒስቶች መቀራረብ ከፍተኛ ትግል ሲያካሂድ የቆየ እንደመሆኑ መጠን፣ ሕብረቱን ለመፍጠር የተደረገውን ጥረት በሙሉ ልብ ይደግፋል። የሕብረቱን አምስት የጋራ አቋሞች፣ ማለትም፣ 1/ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ዋና ዋና ቅራኔዎችና የጊዜው ሁኔታ 2/ ስለወዝአደሩ ፓርቲ አመሠራረት 3/ የዲሞክራሲ ጥያቄ 4/ የመንግሥት ስልጣን ጥያቄ 5/ ስለ መለዮለባሹ ሠራዊትና መርሃ ግብሩን በተግባር ለመተርጐም ከሚታገሉ ድርጅቶችና ተራማጆች ሁሉ ጋር በመተባበር ይታገሳል። እንደዚሁም፣ ማህበራችን፣

ሀ. የኢትዮጵያ ፀረ ቡስት ሃይሎች ሕብረትና የማሌያቸን በይበልጥ መቀራረብ የሚሹ ድርጅቶችና ቡድኖች ሁሉ ለዚህ የጋራ መግለጫና መርሀ ግብር በተግባር መተርጐም፣ በዚህ ትግል ውስጥም ለተራማጆች ሕብረት መጠናከርና ለማሌያች መዋሃድ ያለተቆጠበ ድጋፍ እንዲሰጡና ለዚህም እንዲታገሉ አብዮታዊ ጥሪ ያደርጋል።

ለ. እነዚህ ሕብረቱን ለመፍጠር የተነሱ ተራማጅ ድርጅቶች ሕብረቱ እንዲጠናከር ከሰርጎ ገቦች እንዲጠነቀቁ፣ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው የሕብረቱን አቋምና መንፈስ ማንጸባረቃቸውን እንዲከታተሉ፣ "ጠባብ ቡድንነት" ወዘተ...ከመባባሱና ተጨባጭ ያልሆኑ የመስመር ጥያቄን ከማሸፍኑ ሂሶች፣ ከአሉባልታና ከሌላም ንዑስ ከበርቴያዊ የትግል ዘዴዎች ተቆጥበው ከሥምምነት መድረስን እንደግብ በማስቀመጥ በዲሞክራሲያዊ የሁለት መሥመር ትግል ለመቀራረብና ሕብረታቸውን ለማጠናከር እንዲታገሉ



አብዮታዊ ጥሪ ያደርጋል።

ሐ. በሕብረቱ ውስጥ ያሉ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የተለየ ተግባራቸውን በመረዳት፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ ማሌያችን ለመሰብሰብ፣ ከወዝአደሩና ከደሃው አርሶአደር ጋር በይበልጥ ለመዋሃድ፣ ወዝአደሩንና ደሃውን አርሶአደር በሳይንሳዊ ርእዮተዓለም ለማስታጠቅ በወዝአደሩ ውስጥ መሠረት የጣለና በርሱም የታቀፈ ሃቀኛ የወዝአደር ፓርቲ ለመፍጠር የሚያደርጉትን ትግል በሙሉ ልብ ይደግፋል።

መ. ማህበራችን ሰፊውን ሕዝብ ለማንቃትና ለማደራጀትም ሆነ በተራማጅ ድርጅቶች መሃል ሃቀኛ ፖለቲካዊና ርእዮተዓለማዊ ትግል እያካሄደ የወዝአደሩን ፓርቲ በፍጥነት ለመመሥረት ሂደቱን ሊያፋጥን የሚችለው መሣሪያ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ባስቸኳይ መለቀቅ ነው ብሎ ያምናል።

## ስለ መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መኢሶን/

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 16ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ለመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መኢሶን/ ያለተቆጠበ የፖለቲካ ድጋፍ እንደሰጠ ይታወሳል።

ከዚያን ወዲህ፣ ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ፣ በሃገራችን በተካሄደው ትግል ውስጥ መኢሶን ማህበራችን የሰጠው ድጋፍ ተገቢ መሆኑን የሚያረጋግጡ ብዙ ተጋድሎዎችን በግንባር ቀደምትነት አድርጓል። በዚህ ዓመት፣ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ከሌሎች አብዮታዊያን ጋር በርእዮተዓለምና በፖለቲካ መሥመር ትግል ኢህአፓ ሙሉ ለሙሉ ተጋልጦ እንዲተፋ፣ ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በብዛት እንዲፈልቁ፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የወዝአደር፣ የጭቁን ብሄረሰቦች ንቅናቄዎች እንዲያብቡና እንዲጠናከሩ፣ በጠቅላላ የአብዮቱ ሰፈር ጥራትና ጥንካሬን አግኝቶ ወደፊት እንዲገሰግስ መራራና የተወሳሰበ የፖለቲካ ትግል በግንባር ቀደምትነት አካሄዷል። በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ውስጥ፣ በቀበሌ ማህበራት፣ በወዝአደሮች፣ በሴቶች፣ በወጣቶች ድርጅቶችና አካባቢያቸ ከበማራቸው ታጋይ ጓዶች መሃል ብዙ አባሎችና ደጋፊዎች "ለነቃ ለተደራጀና ለታጠቀ ሕዝባዊ አመጽ" በሚለው መሥመር ስር ተሰልፈው አብዮቱን ሲያገለግሉ በትግል ሜዳ ላይ ተሰውተዋል። ብዙዎቹ በአድሃሪው ቢሮክራሲ አሻጥር ታስረዋል፤ ተገርፈዋል፣ ተሰቃይተዋል፣ ከሥራ ተባረዋል። ነገር ግን ይህ ሁሉ መኢሶንን በይበልጥ በትግሉ እንዲገፋ፣ የወደቁትን ጓዶችን የትግል አርማ ይዞ በይበልጥ ወደፊት እንዲጓዝ ገፋፋው እንጂ አላዳከመውም። በሰፊው ሕዝብ፣ ማለትም በወዝአደሩ፣ በአርሶአደሩ፣ በመለዮለባሾች፣ በወጣቶችና

በሴቶች፣በሃገር ወዳድ ምሁራንና መኮንኖች፣በጭቁን ብሄረሰብ ታጋዮች ዘንድ ይበልጥ ተቀባይነትን አስገኘለት እንጂ አድሃሪያች እንደተመኙት መኢሶን በአድሃሪያን ጥይት ከሚረገፉት አባላቱና ደጋፊዎቹ ጋር አልወደቀም::

በዚህ ዓመት መኢሶን የሰፋ ብሄራዊ ኮንፈረንስ አድርጎ በተሳካ ሁኔታ መደምደሙን አስታውቋል::በዚህ ኮንፈረንስ ላይ መኢሶን ያሳለፋቸው ውሳኔዎች፣በተለይ የተራማጆችን ሕብረት ስለማጠናከር አስፈላጊነት፣ስለዲሞክራሲያዊ መብቶች አጣዳፊነት፣በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ላይ ስላለው የአብዮታዊ ሂስ አቋም፣የኢትዮጵያ አብዮት ከዓለም ተራማጅና ሶሻሊስት አገሮች ስለሚያስፈልገው ድጋፍና በአብዮቱ ውስጥ በራስ መተማመን የሚለው መርህ ስላለው ሚና የተጠቀሱት፣መኢሶን የሰፊውን ሕዝብ ትግል በግንባር ቀደምትነት ለማገልገል የገባውን ቃል ኪዳን የማያጥፍና ለዚህም ያለምንም መታከትና አድርባይነት የሚታገል አብዮታዊ ድርጅት መሆኑን በድጋሚ ያረጋግጣሉ::

በዚህም የተነሳ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በትግሉ ሜዳ በሰማእትነት የወደቁትን የመኢሶን ጓደኞችና የሌሎችንም አብዮታዊያን የትግል አርማ ይዞ ለመጓዝ ቃል ኪዳኑን እያደሰ፣ለመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ያለውን ሙሉ ድጋፍ እንደገና ያረጋግጣል::አምና እንዳደረገው ሁሉ፣ዘንድሮም ለዚህ ታጋይ ማርክሲስት ሌኒኒስት ንቅናቄ ዓለም አቀፍ አጋሮችና ድጋፎች ለማስገኘት የሚታገል መሆኑን በድጋሚ ይገልፃል::

እንዲሁም ማህበራችን ባሁኑ ሰዓት መኢሶን የሚያስተጋባውን ትክክለኛ አብዮታዊ መሥመር፣ማለትም፣በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ላይ ያለውን የአብዮታዊ ሂስ አቋም፣የዲሞክራሲያዊ መብቶችን አጣዳፊነት፣የውስጥና የውጭ ጠላቶች ተጣምረው ስለመገኘታቸውና እነዚህንም አንዱ ዛሬ ሌላው ነገ ሳይባል ለመደምሰስ ስለመነሳት፣ለውጭ እርዳታ ተገቢ ትርጉምና ቦታ ሰጥቶ ዋናውን መመሪያ በራስ መተማመን ስለማድረግ፣በአድሃሪው ቢሮክራሲ ላይ ምህረት የለሽ ዘመቻ ማካሄድና በሰፊው ሕዝብ ላይ ብቻ እምነት ስለመጣል፣በአሁኑ ጊዜ በለጥናና ተለቀ ግዳጅ ላይ በመሰማራት ላይ ላለው ሕዝባዊ ሠራዊት ከአድሃሪው ቢሮክራሲ መላቀቅና አብዮታዊ አመራር ማግኘት አስፈላጊነት፣እንዲሁም ለኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ መፍትሄው በአብዮታችን ወደፊት መግፋት፣በነፃ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝባዊ አመጽ አማካይነትና በረጅም ጊዜ መራራ ትግል ለመወገድ መቻልና የመሳሰሉትን አብዮታዊ አቋሞች እንደራሱ አቋሞች አርጎ ይመለከታቸዋል:: ከመኢሶንና ከሌሎች አብዮታዊያን ጋር ሆኖም ይታገላቸዋል::በዚህ አንፃር በሰፊው ሕዝብ ይበልጥ እየታቀፈ መምጣቱ ያስደነገጣቸው አድሃሪ ሃይሎችና አድርባዮች በመኢሶን ላይ የሚያደርጉትን የማጥላላት ዘመቻና ሊያደርሱበት የሚቃጡትን ጥቃት ማህበራችን በጥብቅ ያወግዛል::



### ስለ ብሄረሰብ ጥያቄ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ከዚህ በፊት እንዳደረገው አሁንም ቢሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ጭቁን ብሄረሰቦች በሙሉ እስከመገንጠል ድረስ ያላቸውን የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብት ያለማወላወል የሚያውቅ መሆኑን በተደጋጋሚ ያረጋግጣል::በዚህ አንፃር በዚህ ጥያቄ ላይ ትክክለኛ አቋም ከወሰዱትና የብሄረሰቦችን ሙሉ መብት ከሚቀበሉት ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶችና እንዲሁም ከተራማጅ ብሄረሰቦች እንቅስቃሴዎች ጎን በመሰለፍ ይህ ጥያቄ አብዮትንና ዓለም አቀፋዊነትን በተመረከዘ ዲሞክራቲክ መንገድ እንዲፈታ ይታገላል::

#### ሀ/ ስለ ኤርትራ

የኤርትራ ሕዝቦች የሃይለ ስላሴ መንግሥት ጭኖባቸው የነበረውን ፋሺስታዊ አገዛዝና ፊውዳሊዝምን በኤርትራ ውስጥ ለማጠናከር ያደረጋቸውን ጥረቶች በመቃወም ያካሄዱት የነበረው ትግል ዲሞክራቲክ ይዘት እንደነበረው የማይታበል ሃቅ ነው::ስለሆነም በዚህ አንፃር ማለትም በዲሞክራቲክ ይዘቱ የኤርትራ ሕዝቦች ትግል የኢትዮጵያ ተራማጆችን ድጋፍ አግኝቶ ነበር::ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮት መፈንዳት በኤርትራም ጭምር የመደቦችን የሃይል አሰላለፍ ማሸጋሸግ በማስከተሉ በኢትዮጵያ አብዮት መፈንዳትና ወደፊት መምጣት የበረገጉት ድሮ ከሃይለ ስላሴ ጋር እጅና ጓንቱ ሆነው የኤርትራን ጭቁን ሕዝቦች ያስጨፈጭፉ የነበሩት የኤርትራ አድሃሪ መደቦች በገፍ ከኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባሮች ጋር በመደባለቅ ለትግሉ ፍጹም ፀረ አብዮታዊ ይዘት ሰጥተውታል::ማለትም የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባሮች ትግል የነበረው ዲሞክራቲክ ይዘት ከሽፎ፣አሁን እነዚህ ግንባሮች ከፋሺስቶችና ከአድሃሪያን ጋር የሚተባበሩና በኢምፔሪያሊስቶች ሥር የሚተዳደሩ ፍጹም ፀረ አብዮታዊ ድርጅቶች ሆነዋል::የኤርትራን ጭቁን ሕዝቦች ጥቅም መንከባከቡን ትተው ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና ለአድሃሪ አረብ ገዥ መደቦች ምንደኛ በመሆን፣ሥራዬ ብለው የያዙትን የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች ነፃ የሚያወጣውን በመካሄድ ላይ የሚገኘውን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት እየተዋጉ ናቸው:: ስለሆነም በኤርትራ የሚካሄደው ትግል የብሄራዊ ነፃነት ትግል ሳይሆን በአብዮትና በፀረ አብዮት መሃል የሚካሄድ መራር ጦርነት ሆኗል::ይህ ሃቅ የሚገለጸው ተገንጣዮቹ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ጋር በፈጠሩት ጥብቅ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን፣የኤርትራ ተራማጆችንና ማርክሲስት ሌኒኒስቶችን ማለትም "መንካ" ብለው የሚጠሩትን የድርጅቶቻቸውን ግራ ክንፍ የሆኑትን ኢሰብአዊና ፋሺስታዊ በሆነ መንገድ መጨፍጨፋቸውም ነው:: የዚህ አይነት ሁኔታ መፈጠር የኢትዮጵያ ተራማጆች ለኤርትራ ግንባሮች ከዚህ በፊት ይሰጡት የነበረውን ድጋፍ ነፍገው በአሁኑ ወቅት እነዚሁ በማያዳግም ሁኔታ

እንዲደመሰሱ ይታገላሉ፡፡በዚህ አኳያ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛ ጉባዔ የሚከተለውን ውሳኔ ያሳለፋል፡፡

1. የኢትዮጵያ አብዮት ለኤርትራ ጭቁን ሕዝቦች ዲሞክራሲንና ነፃነትን ለማምጣት የሚያስችል ከመሆኑም በላይ፣የኤርትራን ሕዝቦች አቁራምታቸውና አራቁታቸው ከነበረው የፊውዳልና ኢምፔሪያሊስት ቀንበር ነፃ የሚያወጣ ነው፡፡ስለሆነም የኤርትራ ጭቁን ሕዝቦች ከኢትዮጵያ ለመገንጠል አይሹም፣ጥቅማቸውም አይደለም፡፡በአሁኑ ወቅት ኤርትራ እንድትገነጠል የሚፈልጉት የኤርትራ ጭቁን ሕዝቦች ሳይሆኑ፣በዚሁ አጋጣሚነት የኢትዮጵያን አብዮት ለማጥቃትና ለመታገል የሚፈልጉት የኤርትራ ገዥ መደቦች፣የአካባቢው አድሃሪ አረብ መንግሥታትና ኢምፔሪያሊስቶች ብቻ ናቸው፡፡በመሆኑም በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ባሁኑ ወቅት ኤርትራን ለመገንጠልና የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ የሚሞክሩትን ጥረቶችንና ትግሎችን በሙሉ ያወግዛል፣ከኤርትራና ከሌላ ኢትዮጵያ ተራማጆች ጎን በመሰለፍ ተገንጣይ የኤርትራ ድርጅቶችን አጥብቆ ይታገላል፡፡

2. የኤርትራ አድሃሪ ተገንጣይ ድርጅቶች፣በተለይም ኢ.ኤል.ኤፍና የኦስማን ሳላህ ሳቤ ቡድን፣ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፣አድሃሪ አረብ መንግሥታት፣ከተበፋው ለዘውዱ ቡድን ኢ.ዲ.ዩና ከቀኝ ክንፍ የንዑስ ከበርቴ ቡድን ኢህአፓ ጋር ያላቸውን ጥብቅ ግንኙነትና በጋራ የሚሸርቧቸውን ፀረ አብዮት ሤራዎችን በጥብቅ ያወግዛል፡፡

3. በኤርትራ አድሃሪያንና ተገንጣይ ቡድኖች ላይ የማያወላውል አብዮታዊ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ ይደግፋል፣በተለይ ኢ.ኤል.ኤፍና የሳለህ ሳቤ ቡድን እንዲደመሰሱ ይታገላል፡፡ነገር ግን የሚወሰዱት ማንኛውም ወታደራዊ እርምጃዎች ውጤት እንዲያስገኙ የፖለቲካ ንቃት ስለሚያስፈልግ ከዚህ አካባቢ የሚወሰዱት ወታደራዊ እርምጃዎች በሙሉ በአብዮታዊ አመራር ስር መሆን እንዳለባቸው ያሳስባል፡፡

4. የኤርትራ ሃቀኛ ተራማጆችንና ማርክሲስት ሌኒኒስቶችን የሚጨፈጭፉትን አድሃሪ ተገንጣይ ቡድኖች ማለትም ኢ.ኤል.ኤፍንና ፒ.ኤል.ኤፍን በዚሁ ፋሺስታዊ ድርጊታቸው እያወገዘ ከኤርትራ ሕዝቦች ጎን በመሰለፍ ይፋረዳቸዋል፡፡

5. ተገንጣይ ድርጅቶች በኤርትራ ውስጥ በሚገኙት ኅዳጣን /ማይኖሪቲስ/ ላይ የሚወስዷቸውን በዘረኛነት የተከሉ ፋሺስታዊ እርምጃዎቻቸውንና እንዲሁም በሃይማኖት ተምክህተኝነት ተመርኩዘው የሚያደርጓቸውን አሰቃቂ



ድርጊቶች በጥብቅ እያወገዘ ለነዚህ ለተጠቁት ኅዳጣን /ማይኖሪቲስ/ የሕዝብ ክፍሎች ጥበቃ እንዲደረግ ያሳስባል፡፡

6. የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች የኤርትራን ታሪክ ለመጠምዘዝ የሚያደርጉትን ከንቱ ሙከራ እየተቃወመ፣ተገንጣዮቹ የደቡቡን ሕዝብ በዝቅተኛ ደረጃ ከነርሱ በታች በማስመሰል የሚነዙትን አድሃሪ ፕሮፓጋንዳ ያወግዛል፡፡

7. በአንድ በኩል በኤርትራ አድሃሪያን ላይ አብዮታዊ የሆነ ወታደራዊ እርምጃ ሲወሰድ በሌላ በኩል ከኤርትራዊያን ተራማጆች ጋር፣(ከተገንጣይ ድርጅቶች ውስጥ ያሉትንም ተራማጆች ያጠቃልላል)፣በመተባበር ለኤርትራ ጥያቄ ዲሞክራቲካዊና ሰላማዊ መፍትሄ እንዲገኝ ከፍተኛ ጥረት እንዲደረግ ያሳስባል፡፡

8. በሲ.አይ.ኤ ሰለጥነው መሀል አገር ሰርገው በመግባት በተራማጆች፣ወዝአደሮች፣የቀበሌ ማህበራት ሠራተኞች፣ምሁራን፣ወዘተ... ላይ የግድያ ድርጊት በሚፈጽሙት የኢ.ኤል.ኤፍ ፋሺስታዊ አፋኝ ቡድኖች ላይ ምህረት የለሽ የማያወላውል አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይጠይቃል፡፡

9. የኤርትራን ሕዝቦች ጥቅም መንከባከብ፣የዕለት ችግሮቻቸውን ማቃለል፣በጦርነቱ ሳቢያ ለተጎዱት አስቸኳይ እርዳታና የመቋቋሚያ ድጋፍ እንዲሰጥ ማድረግ አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን በዚህ አኳያ ከፍተኛ ጥረት እንዲደረግ ያሳስባል፡፡የኤርትራን ሕዝብ ጥቅም፣ሕልውናና፣ንብረትና ሕይወት የሚፃረሩ ወታደሮችና ባለ ስልጣኖች ላይ የማያወላውል አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይጠይቃል፡፡

### ለ/ ስለ አፋር ብሄረሰብ

በአፋር ብሄረሰብ ንቅናቄ የሚመራውን ተራማጅ የአፋር ሕዝቦችን ትግል በመደገፍ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛው ጉባዔ፡—

1. በዚህ ዓመት በገዋኔ ከተማ ተሰብስበው የነበረት የአፋር ሕዝብ ተወካዮች ያሳለፉት ውሳኔና ያቀረቧቸው ጥያቄዎች አስቸኳይ ፍጻሜ እንዲያገኙ ይጠይቃል፡፡በተለይም የአፋር ሕዝቦችን በክፍለ አገር ደረጃ የማጠቃለሉ ጉዳይ ካሁኑ እንዲጀመር፣ያሳስባል፡፡
2. በአፋር ብሄረሰብ ንቅናቄ አማካኝነት የአፋር ሕዝብ እንዲታጠቅ ይጠይቃል፡፡

3. የአፋር ብሄረሰብ ንቅናቄን የሚያጠቃውንና የኢትዮጵያን አብዮት የሚቃወመውን በሱልጣን አሊ ሚራ በሚመራው ቡድን ላይ ያለውን ተቃውሞ እያሰማ በርሱ ላይ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይጠይቃል::

### ሐ/ ስለሌሎች ብሄረሰቦች

ለኦሮሞ ሕዝቦች እኩልነትና ዲሞክራቲክ መብቶች የሚታገለውን በቅርቡ የተቋቋመውን የኦሮሞ ብሄረሰብ ዲሞክራቲክ ንቅናቄ /ኦብዲን/ የአውሮፓ ማህበር እየደገፈ፣በሚያደርጋቸው ትግሎች ከርሱ ጎን እንደሚቆም ያስታውቃል፣ እንዲሁም በቅርቡ ለተቋቋመው ለሃዲያ ብሄረሰብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄም ተመሳሳይ የሆነውን ድጋፉን ያቀርባል::ሌሎች ብሄረሰቦች ለእኩልነታቸው ለመታገል እየተደራጁ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ ተገቢ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማህበራችን አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል::

### መ/ የምዕራብ ሶማሊ ነፃ አውጪ ግንባር ስለተሰኘው ሰርጎ ገብ ድርጅት

አድሃሪው የሶማሊ መንግሥት የኢትዮጵያን አንድ አምስተኛ መሬት ቆርሶ ለመውሰድ ባለው ከንቱ ምኞት " የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ ግንባር " የተሰኘውን አሻንጉሊት ድርጅት በማቋቋም የዚህን ድርጅት ቅጥረኞች እያሰለጠነ በሶማሊ መደበኛ ሰራዊት አባሎች መሪነት ወደ ኢትዮጵያ ሠርገው እንዲገቡ በማድረግ የጭቁኑን ሕዝብ ጸጥታ እንዲያውኩና አብዮቱን እንዲያዳክሙ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል::ይህ አድሃሪ ድርጅት በደቡብና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኙትን ጭቁኖች ጥቅም የሚፃረር ከመሆኑም በላይ የሚጠቀምበት ፕሮፓጋንዳ ፍጹም ዘረኛና በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ማህበራችን ይህን ድርጅት በጥብቅ እያወገዘ የሚወስዱበትን አብዮታዊ የሆኑ ወታደራዊ እርምጃዎች ይደግፋል::እንደዚሁም በደቡብ ምስራቅ ሰርጎ ገቦች ላይ የተሟላ ድልን ለመጎናፀፍ የዚህን አካባቢ ጭቁኖች መንከባከብና እነርሱም ነቅተው በሰርጎ ገቦች ላይ ክንዳቸውን እንዲያነሱ ማድረግና ይህንን የሚያደናቅፉ ነፍጠኞችንና አድሃሪ ቢሮክራቶችን ማጋለጥና መቃወም እንደሚያስፈልግ ማህበራችን ያምናል:: ነገር ግን የዚህን አካባቢ ችግር ሠርጎ ገቦች ላይ ብቻ አማካኝቶ፣ሰፊው ሕዝብ ለመብቱና ጭቁናን ለማስወገድ የሚያደርገውን ትክክለኛ ትግል ለማድበስበስና ለማረሳሳት የሚደረገውን የውስጥ አድሃሪያችን ሤራ ነቅቶ መጠበቅና መታገል እንደሚያስፈልግ ማህበራችን ያስገነዝባል:: ይህንንም ሤራ ማህበራችን በጥብቅ ያወግዛል::



### ስለ ሕዝባዊ ሠራዊት ዝግጅት

የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታቸውንና አንድነታቸውን በመሣሪያ የሚፈታተኗቸውን የውጭና የውስጥ ጠላቶች ለመቋቋም የራሳቸውን ወታደራዊ ሃይል በአብዮታዊ አንፃር ማደራጀት እንዳለባቸው ግልጽ ነው::ስለሆነም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገውን ወታደራዊና የትጥቅ ዝግጅት እየደገፈ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቀርባል:—

1. በተቋቋመውና በመደራጀት ላይ የሚገኘው ከአርሶአደሩና ከወዝአደሩ የተወጣጣው ሕዝባዊ ሠራዊት የተተለመለትን አብዮታዊ ዓላማ ለመምታት እንዲችል ዘንድ ይህ ሠራዊት ከቢሮክራቲክ አመራር ተላቆ አብዮታዊ አመራር እንዲሰጠው፣

2. በገጠር በገበሬው ማህበራት የተቋቋሙት የአካባቢው ሕዝባዊ ሠራዊት አባሎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲታጠቁና የመሳሪያቸው ጥራት እንዲሻሻል፣

3. በቀበሌ ወዝአደር ማህበራት፣ለአብዮቱ ጥበቃ ኮሚቴዎችና እንዲሁም ለተራማጅ ድርጅቶች የሚሰጠው መሣሪያ የተሟላ እንዲሆን በተለይም የመሣሪያው ጥራት አይነት እንዲሻሻል::ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ነገር የጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ ከጥር 26/69 ወዲህ ለሰፊው ሕዝብ የትጥቅ ጉዳይ በአስቸኳይ እንደሚሟላ ቃል መግባቱ፣ነገር ግን የትጥቁ ጉዳይ አሁንም ቢሆን የሚፈለገውን ያህል አለመፈጸሙ ነው::በዚህ በኩል ያለው መጓተት ተወግዶ፣እንዲሁም ለሕዝቡ መታጠቅ እንቅፋት የሆኑት ሁኔታዎች ተገልጸው የሰፊው ሕዝብ ትጥቅ በአስቸኳይ እንዲሟላ ይጠይቃል::

### ፀረ አብዮተኞችን ከከተማ ለማጽዳት መደረግ ስላለበት አሰሳ

ከተሞች በአጠቃላይና አዲስ አበባ በተለይ የፀረ አብዮት ቀንደኞችና የአብዮት መሪ ሃይሎች የሚገኙባቸው ቦታዎች ናቸው::ፀረ አብዮተኞች ከከተማ የሚያካሂዱት የቀለበሳ ትግል ለአብዮቱ አደገኛ እንደመሆኑ መጠን፣በከተማ የሚገኘው ፀረ አብዮት መደምሰስ ለአብዮቱ ከአደጋ ወጥቶ ፋታ ማግኘት ነው::ዛሬ በከተሞች የአጥቂነት ቦታ የያዙት ፀረ አብዮተኞች ናቸው:: በከፍተኛ ደረጃ ከሚያካሂዱት የቀለበሳ ሤራ ሌላ፣በአድሃሪው ቢሮክራሲ ተባባሪነት ታጋዮችን አዲስ ሕዝባዊ ሃይሎች ለመቀጨት ከሚያደርጉት ዘመቻ በተጨማሪ በቀጥር ነፍሰገዳዮች አማካኝነት የአብዮቱን ተኪ የለሽ ልጆች እየቀጠፉ ነው::አብዮቱን ወደ አውነተኛ አጥቂነት ለማሸጋገር፣የከተማ ፀረ

አብዮተኞችን ለመምታትና ሕዝባዊ ሃይሎችን ለማጠናከር ከሚያስችሉ አይነተኛ ዘዴዎች አንዱ አብዮታዊ አሰሳና የምንጠራ ዘመቻ ነው።እስከሁን የተደረጉት አሰሳዎች ያጭር ጊዜ ስለነበረ በአሰሳው የማያምኑ አድሃሪ መኮንኖችም ጭምር በአመራሩ ላይ ስለነበሩ፣የተጠበቀውን ውጤት አላስገኘም። የአሰሳው አጥጋቢ ውጤት አለማስገኘት፣የበርካታ ቀጥር ነፍሰ ገዳዮች አለመያዝና የተያዙትም መለቀቅ፣የብዙ የጦር መሣሪያዎች አለመገኘት፣ለፀረ አብዮተኞች የልብ ልብ እንደሰጣቸው የታወቀ ነው። "እንኳን ሹዚ ታንክ መደበቅ እንችላለን" እያሉ የሚያሾፉ ብዙ ናቸው።ስለሆነም፣አሰሳው ግቡን እንዲመታ፣

ሀ. ተራማጅ መኮንኖችንና የነቁ የሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች አመራሩን መያዝ አለባቸው።በአሰሳው ተራማጅ የቀበሌ ማህበራት በቀበሌው የሚገኙ የነቁ ሠርቶ አደሮች፣ ተራማጅ ምሁራንና ወጣቶች በብዛት እንዲሳተፉበት ያስፈልጋል።የአሰሳውም ዓላማ መሣሪያ መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን ቀንደኛ አድሃሪዎችንና ቀጥር ነፍሰ ገዳዮችን በቁጥጥር ስር ለማዋልም ጭምር መሆን ይኖርበታል።

ለ. አሰሳው ባንድ ጊዜ ሁሉንም ከተማ የሚያዳርስ ብቻ ሳይሆን በየቀበሌው የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች አማካይነት ቋሚ ሆኖ መቀጠል ያለበት አሰሳ ሊሆን ይገባል።ለዚህም አድሃሪው ቢሮክራሲ በአብዮቱ ጥበቃ ኮሚቴዎች ላይ የጫነውን ተጽእኖ እንዲያነሳና፣ያልታጠቁት የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች ባስቸኳይ እንዲታጠቁ፣የታጠቁትም ካላቸው የሕዝብ ድጋፍ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ጭማሪ ትጥቅ እንዲያገኙ መደረግ አለበት።

<u>ስለ ጂቡቲ</u>

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛ ጉባዔ የጂቡቲን ነፃ መውጣት ሙሉ በሙሉ እየደገፈ፣

1. ትምክህተኞች የሶማሌ ገዥ መደቦች ጂቡቲን በሚመለከተው በኩል ያላቸውን የመስፋፋት ስሜትን ጂቡቲን በግዛታቸው ሥር ለመጠቅለል ያላቸውን ከንቱ ምኞት በጥብቅ ያወግዛል።

2. የጂቡቲ ተራማጅ ሃይሎችና ሀገር ወዳዶች የጂቡቲን ብሔራዊ ነፃነትና አንድነት ለማስጠበቅ ሃይላቸውን አጣምረው እንዲታገሉ ጥሪውን ያቀርባል።



<u>ስለ ኢምፔሪያሊዝምና የብሔራዊ ነፃነት ጉዳይ</u>

የምዕራብ ኢምፔሪያሊስቶች፣በተለይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም፣በኢትዮጵያ ውስጥ የነበራቸው ግልጽ ተጽእኖ ከሞላ ጎደል ቢወገድም፣ 1/በአድሃሪ ጎረቤት መንግሥታት፣ 2/ኢዲዩ፣ኢሀአፓ፣ኢኤልኤፍ በተባሉ፣ 3/በአድሃሪ መኮንኖችና ቢሮክራቶች ፀረ አብዮታዊ ድርጅቶች አማካኝነት በኢትዮጵያ አብዮት ላይ በውስጥና ከውጭ የጀመሩትን የማጥቃት ዘመቻቸውን በማፋፋም ላይ ይገኛሉ።ከነዚሁ የኢምፔሪያሊዝም ቡችሎች ጋር የሚደረገው ትግል በመሣሪያ ደረጃ መካሄዱ፣በኢትዮጵያ አብዮትና በኢምፔሪያሊዝም መሃል ያለው ቅራኔ ከፍተኛ ደረጃ እንደደረሰና ኢምፔሪያሊስቶች የኢትዮጵያን አብዮት ወደ ኋላ ለመቀልበስ ከመሞከር እንደማይመለሱ ይመሰክራል፣ሆኖም በመጨረሻ ደረጃ ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነውና ከነዚህ የኢምፔሪያሊስት ምንደኞች ጋር የሚካሄደው ጦርነት በአብዮታዊ አመራር ስር ቢውል የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላቶቻቸውን በማያዳግም አኳኋን ለማሸነፍ እንደሚችሉ አያጠራጥርም።

የፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግላችን ከውጭ ሆነው ሃገራችንን በሚያጠቁት ወራሪዎች ብቻ ሳይወሰን፣መሃል አገር የሚገኙትን ምንደኞቻቸውን በተለይም አይነተኛ መሣሪያ የሆናቸውን ቢሮክራሲውን መጨመር አለበት።ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሮክራሲውን አንከባክበው ያሳደጉት ኢምፔሪያሊስቶች እንደመሆናቸው መጠን፣ ባሁኑ ወቅት ዋና ጠላት የውጭ ወራሪዎች ናቸው ተብሎ የኢምፔሪያሊዝም አይነተኛ መሣሪያ የሆነው ቢሮክራሲ የተተወ እንደሆነ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግሉ ስንኩልና ግቡን ለመታ የሚችል እንደማይሆን መታወቅ አለበት።

የፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግሉ ዋና ዓላማ የሃገራችንን ብሔራዊ ነፃነት ማስከበር እንደመሆኑ መጠን የኢትዮጵያ ሕዝቦች በገጠሟቸው ከባድ ችግሮችና እንዲሁም በዚህ አካባቢ በተፈጠረው ውስብስብ ሁኔታ በመጠቀም፣ሌሎችን አገሮች አራቀው በስንት ትግል የተባረሩ ኢምፔሪያሊስቶች ወደ አገራችን ሰርገው እንዳይገቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።ማለትም ሃገራችን ኢምፔሪያሊስቶች የሚቀራመቷት ቅርጫት፣ፉከራቸውን የሚወጡበት መድረክ እንዳትሆን ብሔራዊ ነፃነታችንን ለመጪው ትውልድ አኩሪ በሆነ መንገድ መጠበቅ መቻል አለብን።በኢትዮጵያ ውስጥ ይበልጥ በመመታት ላይ ያለዉ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መልሶ የመንሰራራት አመቺ ሁኔታዎች ስላሉ የማያቋርጥ ፀረ አሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ትግል መካሄድ አለበት።በዚህ አንፃር ጊዜያዊ ወዳጅን ከዘላቂ ወዳጅ፣ሃቀኛውን ከአስመሳዩ አበጥሮ መለየትና ማወቅ ያስፈልጋል።

ብሔራዊ ነፃነታችንን ፍጹም ባናስደፍር ሕዝባችንን በሚያኮራ መንገድ ለማስከበር ከሁሉም ይበልጥ በራስ መተማመን የሚለውን መርህ መከተልና ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።ማለትም ለአብዮታዊ እናት አገሩ ለመሞት ዝግጁ በሆነው ሰፊው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ መመካትና በርሱም እምነት በመጣል

የራስ መተማመንን መርህ በመከተሉ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ መቀስቀስና ለአብዮታዊ ትግልና ስርዓት ማደራጀት ያሻል። በራስ መተማመን በሃገራችን ላይ የሚቃጧውን ማናቸውም የኢምፔሪያሊስቶች የተጽእኖ ሙከራ የሚያከሽፍ ከመሆኑም በላይ ለአገራችን ክብርና ሕልውና ዘላቂና አስተማማኝ ዋስትና ነው።

ስለሆነም ዛሬ አብዮታችን ተከቦ በተለይ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አስተባባሪነት ከየአቅጣጫው በሚጠቃበት ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ጭቁን ሕዝቦች አብዮት የማይነጠል አካል መሆኑን ተገንዝበው ሊረዱ የተነሱትን በሶሻሊስት አገሮችና የአለም አቀፍ ዲሞክራሲያዊና ተራማጅ ሃይሎች ድጋፍ በነፃነት ትግሉ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል። ስለሆነም በዓለምአቀፋዊነት መንፈስ ከሶሻሊስት አገሮችና ከሌሎችም አብዮታዊ ሃይሎች ጋር የሚደረገውን መቀራረብና ግንኙነት ማህበራችን ይደግፋል።

## ስለ ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት

የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ለኢትዮጵያ አብዮት ተከከለና ፈር ይዞ መምጣት፣ ለሰፊው ሕዝብ፣ በንቃት እየጎለመሰና እየተደራጀ፣ በአብዮቱ ውስጥ ይበልጥ መሳተፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉን የኢትዮጵያ ጭቁኖች ይመሰክሩለታል። የጽሕፈት ቤቱ ካድሬዎች በሰፊው ሕዝብ የቀን ተቀን ትግል ውስጥ ገብተው የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ይዘትና ዓላማ፣ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታና የመደብ አሰላለፍ ወዘተ በመግለጽ ያካሄዱት የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ትግል፣ በዚህም ትግል ላይ ተመርኩዘው ለሰፊው ሕዝብ መደራጀት ያበረከቱት አገልግሎት በኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ውስጥ አኩሪ ቦታ የሚያስይዛቸው ነው።

ለጭቁኖች የቆመን፣ ከጭቁኖች ጎን የተሰለፈን፣ የጭቁን መደቦች ጠላቶች እንደሚጠምዱት የታወቀ እንደመሆኑ መጠን የፀረ አብዮተኞች ጥላቻ ምንጭ ያረፈው በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤትም ላይ መሆኑ አይገርምም። የኢትዮጵያ አድሃሪ ድርጅቶችና አድሃሪው ቢሮክራሲ በዚህ ጽሕፈት ቤት ላይ ከፍተኛ የማጥላላት ፕሮፓጋንዳ የነዙት በዚህ ምክንያት ነው። የቀለባሾች መሣሪያ የሆኑት ቀጥር ነፍሰ ገዳዮች ፋሽስታዊ ጥይት በሕዝብ ድርጅት ጓዶች ላይም የተኮሱት በዚህ ምክንያት ነው። እነሲሳይ ሀብቴ በቀጥታ ሲደመስሱት የነበረው፣ እነአለማየሁ ሃይሌ መሊቡን ብቻ የተወከለበት ድርጅት ነው በማለት "ሌሎችም ይግቡበት" ያሉት ያው ከፀረ አብዮት ዓላማ ነበር። እነ ኢህአፓን ሊያስገቡበት የሞከሩት ይህንን ሃቅ በመመልከት ነበር።

የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ጓዶች ቀድሞውን የኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ባበገኙቸው ድሎች ተጠቅመው በሕጋዊው የትግል መስክ ሰፊውን



ሕዝብ ለማገልገል ቆርጠው የተነሱ በመሆናቸው፣ የአድሃሪያኖች የማጥላላት ዘመቻ፣ የአድሃሪው ቢሮክራሲ ተጽእኖ፣ የቀኝ ክንፍ የነውጥ ከበርቴ ቡድን ጥይት ከዓላማቸው ንቅንቅ አላደረጋቸውም። በሰፊው ሕዝብ ታቅፈውና ከርሱም ጋር ሆነው በሚያደርጉት አብዮታዊ ትግል ገፍተውበታል። በዚህም ትግል ውስጥ የመጨረሻውን መስዋእትነት ለመቀበል ዝግጁ በመሆናቸው ከጎናቸው ጓዶች በወደቁ ቁጥር በበለጠ ቁራጥነትና ዝግጁነት የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ አብዮት ማገልገላቸው ባይታለፉ የተፈታ ነው። ማህበራችን፦

ሀ. የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ሰፊውን ሕዝብ ለማንቃትና ለማደራጀት ባደረገው ትግል ከጎኑ ተሰልፏል፣

ለ. የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ካድሬዎች ባደረጉት አብዮታዊ ትግል ውስጥ ከአድሃሪያኖች የደረሰባቸው የማጥላላት ዘመቻ፣ ከአድሃሪው ቢሮክራሲ የተደረገባቸው ተጽእኖና በቀኝ ክንፍ የነውጥ ከበርቴ ከፍል የደረሰባቸውን ጥቃት እያወገዘ ከነዚህ ጠላቶች ጋር ላደረገው ትግል ሙሉ ድጋፉን ይገልፃል፣

ሐ. የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤት ከአድርባይነት ርቆ፣ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን ፈር ሳይለቅ፣ በተሰውለት ታጋይ ጓዶቹ ደም የፀፋቸውን አኩሪ የትግል ገጾች እንዲያድስ ጥሪ ያደርጋል፣

መ. በያዝነው ዓመት በትግሉ መስክ ተሰማርተው ሲታገሉ በአድሃሪያኖች ጥይት ተመትተው የወደቁትን ካድሬዎች ሰፊው ሕዝብ ለዘላለም እንደሚያስታውሳቸውና አብዮታዊውን የትግል አርማቸውን አንስቶ አብዮቱን ለማፋፋም እንደተነሳ ያረጋግጣል።

## ስለ ኢህአፓ

የነቁ አድሃሪያን "ተራማጅ ክበብ" የሆነው ኢህአፓ የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ አብዮት ለማጨናገፍ ከፍተኛ ጥረትና ትግል ያደረገ ፀረ ሕዝብ ድርጅት ነው። ይህ የከሃዲ ምሁራንና የቀኙ ክንፍ ነውጥ ከበርቴ፣ የነቁ አድሃሪያን መጠራቀሚያ የሆነ ድርጅት ለሰፊው ሕዝብ የንቃትና የድርጅት እድገት ከፍተኛ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል።

የሰፊውን ሕዝብ ንቃት ሕሊና ዝቅተኛነት በመጠቀም ባካሄደው የማወናበጃ ትግል ብዙ የሰፊውን ሕዝብ ወገኖችን የተሳሳተ የፖለቲካ መሥመር ስር አሰልፎ ነበር። ሰፊው ሕዝብ ባልተዘጋጀባቸው ግጥሚያዎች ከጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትና ከአድሃሪያቶችም ጋር እያጋጨ አስመትቷል። ሰፊው ሕዝብ እንዳይደ

ራጅ፣ የተደራጀውም በርሱ ቁጥጥር ስር እንዲሆን በማድረግ ከፍተኛ ፀረ ድርጅት ትግሉቸን አካሄዷል::አብዮቱ እየገፋ ሲሄድ፣የኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆች ባካሄዱት የከረረ የፖለቲካና የርእዮተዓለም ትግል መሠረት ወዘ አደሩ በትግሉ በቀሰመው ትምህርት ንቃቱ በለጉለመሰ "ኢህአፓ" ተጋለጠና ተሸንፍ ከሰፊው ሕዝብ ሰፈር ተተፍቷል::ዛሬ ኢህአፓን የሚያሞግሱት "ማርክሲስት ሌኒኒስት" እያሉ የሚያራግቡለት ኢምፔሪያሊስቶችና የኢትዮጵያ መሳፍንት ናቸው::የነቃው የኢትዮጵያ ሠርቶአደር "ቀለበሹ የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ ድርጅት ኢህአፓ ይውደም" በሚል መፈክር ስር ተፍ ተውት ሳይረኩ ሊደመስሱት እየታገሉ ነው::ባንድ ቃል ዛሬ ኢህአፓ በሰፊው ሕዝብ ተተፍቶ በአድሃሪያን የታቀፈ የቀኝ ክንፍ የንዑስ ከበርቴዎች ድርጅት ነው::

ኢህአፓ በሰፊው ሕዝብ ከተተፋ በኋላና በውስጡም የነበሩ የተወናበዱ የሕዝብ ወገኖች እየጣሉት በኒዎአድሃሪያን ከተጥለቀለቀ ወዲህ፣በአጠቃላይ በፖለቲካው መድረክ ተጋልጦ ከተሸነፈ ወዲህ በፖለቲካ መሥመር ማወናበዱን ትቶ በፋሺስታዊ ድርጊቶች ላይ ተሰማርቷል::በገጠር እንዳቋሙ ያስለፈው ሠራዊት ከኢዲዩና ከሌርተራ አድሃሪያኖች ጎን ተሰልፎ የኢትዮጵያን አብዮት መዋጋቱ ብቻ ሳይሆን፣በቢአይኤ ረዳትነት፣በከተሞች ጥቁን የቀበሌ ማህበራት፣የሴቶች ማህበራት መሪዎቻችን፣ታጋይ ወጣቶቻችን፣ሃቀኛ ተራማጆችን ጨፍጭፏል::ዛሬም የአብዮቱን ሃይሎች ለማዳከም በመሠረታዊ ጠላቶቻችን እየታገዘ ፀረ ሕዝብና ፋሺስታዊ ትግሉን ቀጥሏል::

"ኢህአፓ" ዛሬ ከመደብ ጠላቶቻችን ተነጥሎ የማይታይ፣እነርሱ ጉያ ስር ሆኖ በፀረ አብዮትና ፀረ ሕዝብ ትግል ላይ የተሰማራ ፋሺስታዊ ድርጅት ነው::ስለሆነም ኢህአፓን መደምሰስ የኢትዮጵያን አብዮትና ሕዝብ መሠረታዊ ጠላቶች ዓይነተኛ የቀለበሰ መሣሪያ ማሳጣት ነው::ማህበራችን፣

ሀ. የነቃ ወዝአደሮችና ሠር አደሮች፣ተራማጅ ሃይሎችና ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ይህንን ፋሺስታዊ ድርጅት ለመደምሰስ የሚያደርጉትን ትግልና በዚህም አቀጣጫ የሚወሰዱትን እርምጃዎች ሁሉ ይደግፋል::

ለ. ይህን ፋሺስታዊ ድርጅት በዓለም ተራማጅ ሃይሎች ፊት ለማጋለጥ፣ከቀኝ ደና ኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመተባበር በውጭ የሚገኙ የፋሺስታዊው ድርጅት ግብረአበሮች የኢትዮጵያን አብዮት በማጥላላት የሚያደርጉትን ዘመቻ ለማክሸፍ ማህበራችን ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ ወደፊትም በከፍተኛ ደረጃ ፀረ ኢህአፓ ትግሉን ይቀጥላል::



ስለ ሕዝባዊ ድርጅቶች

በአገራችን የኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ያስገኛቸውን ድሎች ተመርኩዘው እያሉ ሕዝባዊ ድርጅቶች እየፈለቁ ናቸው::ሰፊው ሕዝብ በንቃቱ እየጐለመሰ በሄደ መጠን፣እነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶች ከሰርጎ ገብ አድሃሪያኖች እየፀዱ፣የሰፊው ሕዝብ መገልገያዎች እየሆኑ መጥተዋል::

እነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ለኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል የተቀነባበረና አስተማማኝ አመራር የሚሰጠው የነገው ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ምሰሶዎች ናቸው::

እነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣በዛሬው አድሃሪ ቢሮክራሲና በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ቦታ የሚቋቋመው የወደፊት ሃቀኛ ሕዝባዊ መንግሥት ጽንሶች ናቸው::እነዚሁ የዛሬ ሕዝባዊ ድርጅቶች አድገው፣ጠንክረው በወዝአደሩ መሪነት በሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ውስጥ ተሰባስበው የነገው ሕዝባዊ መንግሥት አካሎች ይሆናሉ እንጂ፣አድሃሪው ቢሮክራሲ በተዓምር ጠፍቶ ሕዝባዊ መንግሥትም ከሰማይ ዱብ አይልም::

የዛሬዎቹ ሕዝባዊ ድርጅቶች እንደዚህ አይነት ይዘት ስላላቸው ነው የፀረ ሕዝቦች ፋሺስታዊ በትር ከሁሉም በላይ እነርሱ ላይ የተሰነዘረው::አድሃሪው ቢሮክራሲ ነገ የሚሰባበረት ሃይሎች መሆናቸውን ስለተረዳ ነው ባንድ ወገን እነርሱ ላይ የሚደርሰውን ጥቃት እያገዘ፣በሥልጣኑም እነርሱን የሚጫነው::እንደዚሁም በሌላ በኩል እነዚህን ሕዝባዊ ድርጅቶች ጠላቶቻቸውን እንዳይመቱ እንዳይጠናከሩ እንቅፋት የሚሆንባቸው::የአብዮቱ ወገኖችና ተራማጆች ደግሞ በፊናቸን እነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶች ከላይ የጠቀስናቸውን ይዘቶች ስላሏቸው:—

ሀ. እነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶች ካሁኑም በበለጠ ተራማጅና አብዮታዊ አመራር እንዲያገኙ፣ካሁኑ በበለጠ በየፊናቸው የሰፊውን ሕዝብ ወገኖች እንዲያቅፉ፣

ለ. እስካሁን ባገኙት ሕጋዊ መብትና ሥልጣን ሙሉ ለሙሉ እየተጠቀሙ ለሚቀራቸው መብትና ስልጣን ተጠናክረው እንዲታገሉ፣

ሐ. ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር በሚያደርጉት የቀን ተቀን ግጭት ተገፍተረው እንዳይወድቁና አሸናፊ እንዲሆኑ በሚያደርጉት ፀረ አድሃሪና ፀረ ቢሮክራሲ ትግል ሁሉ ከጎናቸው እንቆማለን::

ሠ. እስካሁን ድረስ በቀበሌ ማህበራትና በሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ
ሲታገሉ በአድሃሪያች ለተገደሉ ጓደቻችን፣ሲታገሉለት የወደቁውን አርማ
አንስተን እንደነሱ በትግል በመስዋእትነት ለመጓዝ ቁርጠኑ መነሳታች
ንን እናረጋግጣለን::በተለይም የመኢሠማ ሊቀመንበር የነበረው የጓድ
ቴዎድሮስ በቀለና የሌሎች ታጋይ ወዝአደሮች አሬያነት ህያውነቱን
እንደያዘ ይቆያል::ጓድ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን መዝአደር አውነተኛ
ጥያ ጥቅም ሊያስጠብቅ የሚችል ድርጅት ለመፍጠር ከቀድሞው አድሃሪ
የኢሠአማ አመራርና ከቀኝ ክንፉ የንዑስ ከበርቴ ድርጅት ኢህአፓ ጋር
ያደረገውን ትግል ማህበራችን ሲያስታውሰው ይኖራል፣እነ ጓድ ቴዎድ
ሮስ...የተሰዉለት መኢሠማ የወዝአደሩን አንቀሳቃሴ ከመሠረቱ እንዲ
ያጠናክር ማህበራችን ይታገላል::

— ስለ ሴቤስን

አድሃሪ ስርዓቶች በሴቶች ላይ የጣሉትን የጭቁና ቀንበር ለመታገልና
ጭቁን ሴቶችን ለነፃነታቸውና ለእኩልነታቸዉ እንዲታገሉ ለብሄራዊ ዲሞክራቲክ
አብዮት አንድ ሃይል እንዲሆኑ ከብዙ ግዜ ጀምሮ እየታገሉ ናቸው::የአብዮ
ቱ ዉሎች በከፈቷቸው መስኮች ብቻ ሳይወሰኑ በሰው " ታጋይ ኢትዮጵያዊት "
ን በማውጣት ጭቁን ሴቶችን በተከከለና አብዮታዊ ትግል ለማሰለፍና ፀረ
ሴት ድርጅትና ፀረ አብዮት የሆኑትን የኢህአፓን እነስታይ ክንፍ በማጋለጥ
ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል::የኢትዮጵያ ጭቁን ሴቶች ትግል በደረሰበት
ደረጃ ሴቶችን በበለጠ ለማንቃትና ለማደራጀት የሴቶችን አብዮታዊ ድርጅት
እንዲመሠረት ለማገዝና በዲሞክራቲክ መብቶች አለመኖር በሴቶች መደራጀት ላይ
ባስከተለው መጓተት በየበታው ያሉ ተራማጅ ሴቶችን ቡድኖችን ለማስተባበር
በታጋይ ኢትዮጵያዊት አካባቢ የተደራጁ ሴቶች አንድ መርሃ ግብር በማዉጣት
የሴቤስንን ሕልውና አስታውቋል::

በአዉሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የዚህን መርሃ ግብር ይዘት
ከመረመረ በኋላ፣

1. በጊዜው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ትክክለና አቋሞችን በመውሰድ
ሴቶችን ለብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ለነፃ ለተደራጀና ለታጠቀ የ
ሕዝብ ትግል ለማሰለፍ በመታገሉ፣

2. ሴቶች ትግላቸውን የሚያቀናብሩበትን አብዮታዊ ድርጅታቸውን በመፍጠር
የማያቋርጥ ትግል በማድረጉ፣



3. በሴቶች ጥያቄ ላይ ትክክለኛ መሥመር በመተለም ሴቶች በሶሺያል፣በፖለ
ቲካ፣በኢኮኖሚ ኑሮ እኩልነት እንዲኖራቸውና የአድሃሪ ባህሎች በሴቶች
ላይ የሚያስከትሉትን ተጽእኖ በመታገሉና በልሳኑ በታጋይ ኢትዮጵያዊት
በጭቁን ሴቶች መሃል የሚያደርገውን ቀስቀሳ አብዮታዊነት በማየት፣ይህ
ጉባዔ ለሴቤስን ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል በሚያደርገውም ትግል ማህበራችን
ከጎኑ ይሰለፋል::

ስለ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮት በመጨረሻው ደረጃ የሰፊ
ውን ሕዝብ ኑሮ ደረጃ ማሻሻልንና የአገሪቷን ብልጽግናን ማዳበር ቢሆንም፣
ባሁኑ ውስብስብ የአብዮት ወቅት በተለያዩ የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊና አገ
ሪቷም በአብዮት ሳቢያ በተፈጠሩት ሁኔታዎች ምክኒያት በተለይ የከተማው
ሕዝብ ኑሮ እየቀረቀዘ በመሄድ ላይ ይገኛል::ይህ ብቻ አይደለም::ወደ
ገጠርም ስንመጣ የመሬት አዋጁ ሰፊውን አርሶ አደር ከፊውዳል ምዝበራ ነፃ
በማውጣቱ አርሶአደሩ ከሚያመርተው አንዱን ክፍል ወደ ገበያ ለማውጣት ሲ
ችልና ሲፈልግ ለእርሻ ምርቱ ለውጥ የሚሆን እንዱስትሪያል ሸቀጥ ስለሚያ
ቁርበለት የሃገሪቷ ኢኮኖሚ ሊዛባ ከመቻሉም በላይ፣በእርሻና በኢንዱስትሪ
ማለትም በከተማና በገጠር መሃል ያለው ግንኙነት እንዳይበጠስ ያሰጋዋል::
የዚሁ አይነት ሁኔታ መቀጠል በፖለቲካ አገፀር ለፀረ አብዮት አመቺ ሁኔታ
ከመፍጠሩም በላይ፣በኢኮኖሚያዊ ደረጃ የገበረውን እርሻ ወደ ተፈጥሮ ኢኮኖ
ሚ /ናቹራል ኢኮኖሚ/ በመመለስ የርባታ ሃይሎች ውድቀት ሊያስከትል እንደ
ሚችል መታወቅ አለበት::

በሸቀጥና ምርት ማከፋፈያ ዘርፍ ለተከሰተው፣በዚሁ ለሚተዳደረው የሕዝ
ባችን ክፍል ለደረሰበት የኑሮ ማሽቆልቆል አንዱ ምክኒያት ባለም አቀፍ ደ
ረጃ ያለው የኢኮኖሚ ቀውስና የዋጋ መዛባት ቢሆንም ከዚህ ሁኔታ መፈጠር
ተጨማሪ የአገር ውስጥ ምክኒያቶች እንዳሉና ኢትዮጵያን የገጠሟት ኢኮኖሚያ
ዊ ችግሮች እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ ከአብዮቱ ሂደት ጋር የተያያዙ መሆ
ናቸውን በመረዳት፣ይህን ሁኔታ ለማሻሻል አስቸኳይና አጣዳፊ እርምጃዎች እ
ንዲወሰዱ በአዉሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛው ጠቅላላ ጉባዔ
ያሳስባል::በዚሁ አገፀር በአዉሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 17ኛ ጠቅ
ላላ ጉባዔ

1. የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ መዋቅር ለማሻሻልና ለሰፊው አርሶአደር የሚቀር
ቡትን የኢንዱስትሪ ሸቀጦች በመጠኑም ቢሆን እንዲጨምሩ የሚያስችል ያ
ጭር ጊዜ ኢኮኖሚ እድገት ፕላን ወጥቶ ባስቸኳይ ሥራ ላይ እንዲውል፣

2. ምርት እንዲበላሽ፣እንዲስተጓጎል በሚያሻጥሩትና ወዝአደሩ ለምርት እድገት የሚያካሂደውን ትግል በሚያፍኑት ቢሮክራቶች ላይ ጥብቅና አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድ፣

3. የዋጋው ቁጥጥርና ተመን ሥራ ላይ እንዳይውል እንቅፋት በሆኑት ነጋዴዎችና ቢሮክራቶች ላይ ጥብቅ እርምጃ እንዲወሰድ ይጠይቃል::



## ድርጅታዊ ውሳኔዎች

### በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለመደራጀት

የኢትዮጵያ ወጣቶች በአገር ውስጥና በአገር ውጭ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለመደራጀት ጉዳይ ማህበራችን በተደጋጋሚ ሥራ ላይ እንዲውል ጥሪውን እንዳቀረበ ይታወሳል::በየወቅቱም ለተደራጁና በመደራጀት ላይ አብዮታዊ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ጋር ግንኙነት መስርቶ በዓለም አቀፍ በስመደራጀቱ ጉዳይ ላይ ውይይት እንዲከፈት ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል::

ሆኖም በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ በመካከለኛው ምስራቅና አፍሪካ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት እስካሁን በአህጉር ደረጃ በአንድ አጠቃላይ ድርጅት ባለመደራጀታቸው፣አገር ቤት ያለው የተማሪ እንቅስቃሴ ውስጥ፣በአብዮታዊና በፀረ አብዮት ቡድኖች መካከል በመካሄድ ላይ ከነበረው ትግል አሸናፊ ሆኖ የወጣው አብዮታዊው ቡድን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብቻ በመደራጀቱ፣ሴቶች በየአህጉሩ ማህበር እንዲቋቋሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ ማህበር ባለመመስረታቸው በዓለም አቀፍ የመደራጀቱ ተግባር በሃሳብ መለዋወጥ ተወሰኗል::

የዚህን ጉዳይ ፍጹም አስፈላጊነትንና አጣዳፊነትን በመገንዘብ፣የተደረበትን መሰረታዊ ስምምነት በመረዳት፣ያለፈው የአ/ኢ/ተ/ማ የሥር አስኪያጅ ኮሚቴ በዲሴንበር ወር መጨረሻ ላይ ስብሰባ እንዲጠራ ያቀረበውን ሃሳብ ሙሉ ለሙሉ በመደገፍ፣ከ7 እስከ 14/77 በሉዛን ከተማ የተሰበሰበው የአ/ኢ/ተ/ማ 17ኛው ጠቅላላ ጉባዔ መጪው የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ይህንን ጉዳይ በሥራ ላይ እንዲያውለው ያሳስባል::

በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ አገራችን የሚካሄደው አብዮት ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ በሚሊዮን የሚቆጠሩት ጭቁን ሴቶች መደራጀት አለባቸው:: የሴቶች መደራጀት የአብዮቱ ወሳኝ እንደመሆኑ መጠን በአሁኑ ወቅት የሴቶች መደራጀት ከዋና ዋናዎቹ ጥያቄዎች አንዱ ነው::ስለሆነም፣በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበርና እንዲሁም ቅርንጫፍ ማህበራት በአካባቢያቸው የሚገኙትን ሴቶች እንዲደራጁና የተደራጁትም እንዲጠናከሩ ተለቅ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ማካሄድ አለባቸው::በተጨማሪም በሚያወጧቸው ጽሑፎች ላይ የሴቶችን ጥያቄ እያነሱ ብዙ ቅስቀሳ እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀርባል::

<u>ስለ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኀከራቢያዊ ሃይሎች</u>

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፃነት ትግል ያበረከተው አኩሪ ትግል፣በታሪክ ከፍተኛ ቦታ እንደሚይዝ እሙን ነው::በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ አብይ ቦታ ይዞ ከሰፊው ሕዝብ ጠላቶች ይህ ነው የማይባል ጥቃት ሲወርድበት በቆራጥነት የትግሉን ባንዲራ አንግቦ ወደፊት በመጓዝ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝናን ያተረፈው ያገር ቤት እንቅስቃሴ ነበር::

ሆኖም ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ያገር ቤቱ የተማሪ እንቅስቃሴ መዋቀር ሳይኖረው እንደተበታተነ ይገኛል::በጥር ወር 1969 ከየካቲት እንቅስቃሴና ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያን ሁኔታ አይነተኛ ካደረገው የሁለት መሥመር ትግል የፈለቀ ሰፊውን ተማሪ ለመሰብሰብ ታጥቆ የተነሳ ድርጅት የፖለቲካ አቋም መግለጫውን ማውጣቱን በማስታወስ፣

— ይህ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኀከራቢያዊ ሃይሎች የፖለቲካ አቋም መግለጫ ፍጹም አብዮታዊ መሆኑን በማመን የአ/ኢ/ተ/ማ ሙሉ ድጋፉን ይሰጠዋል::ይህንንም ድጋፍ በተግባር እንደሚያስመሰክር ይተማመናል::

— በኖቬንበር ወር መጨረሻ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለመደራጀት በአ/ኢ/ተ/ማ ስብሰባ ስለሚጠራ፣ይህ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኀከራቢያዊ ሃይሎች በዚህ በዓለም አቀፍ ስብሰባ ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ ጥሪ እንዲደረግላቸው መጨውን የአ/ኢ/ተ/ማ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ያሳስባል::

<u>ስለ አ/ኢ/ተ/ማ ልዩ ጽሕፈት ቤት</u>

ማንኛውም አብዮት ድሉን እንዲጐመታ ከተፈለገ ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ ማግኘት ይኖርበታል ይህን ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ ለማግኘት ተራማጅ ሃይሎችን በውጭ አብዮቱን ማስተዋወቅና ድጋፍ እንዲያገኙ መጣር አለባቸው::

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት ባጠቃላይ ሲታይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቸኝነት ያጠቃዋል::ለዚህ ብቸኝነት ዋና ዋና ምክንያቶች:—

1. የአብዮቱ ጠላቶች ማለትም ኢምፔሪያሊስቶች፣አድሃሪ የጎረቤትና የአረብ አገሮች፣ኢዲዩ፣ኢህአፓ/ፌዴረሽን፣ኢኤለኤፍ፣ፒኤለኤፍ እንዲሁም አድሃሪ ድርጅቶች አብዮቱን ብቸኛ አድርጎ ለመቀልበስ በውጭ የሚያካሂዱት የበሬ ወለደ ፈጠራ ወሬዎችና የቀለበሳ ፕሮፓጋንዳዎች በውጭ



የፈጠረው ውዥንብርና መወናበድ፣

2. እላይ ከተጠቀሱት አድሃሪ ሃይሎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመተባበር ያለአንዳች ተቃውሞ ይህ ውዥንብር እንዲቀጥል የሚተባበሩ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች፣

3. ተራማጅ ሃይሎች አብዮቱን ለማስተዋወቅና ድጋፍን እንዲያገኙ የሚያካሂዱት ትግል የተፈለገውን ያህል ውጤት ባለመስጠቱ ነው::

ማህበራችን በኢትዮጵያ አብዮት ላይ በውጭ የሚካሄደውን ፀረ አብዮት ፕሮፓጋንዳ ለመቋቋምና የአብዮቱን ትክክለኛ መልክ በማስታወቅ ዓለም አቀፋዊ ድጋፍን ለማስገኘት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል::ለዚህም ጽሁፎችን በውጭ አገር ቋንቋ በማውጣት በውጭ ለሚገኙ ተራማጅ ድርጅቶችና ግለሰቦች ለማሰራጨት ሞክሯል::ሆኖም ባንድ ወገን ከአብዮቱ እድገት ጋር በመያያዝ በውጭ የሚካሄደው የቀስቀሳ ፕሮፓጋንዳ እየጨመረ በመሄዱ በሌላ ወገን የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውም ሆነ የመጽሔት ቦርዱ ጽሑፎችን በውጭ ቋንቋ እያወጡ ለማሰራጨት የጊዜ እጥረትና የሃይል ማነስ ችግሮች ስላለባቸው አብዮቱን በከፍተኛ ደረጃ ለማስተዋወቅ የዚህን ሥራ እጅግ አስፈላጊነት በመረዳት ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ይህን ተግባር የሚያከናውን አንድ ልዩ ጽህፈት ቤት እንዲቋቋም ባቀረበው ሃሳብ ላይ ቤቱ ሙሉ ለሙሉ ተስማምቶ ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ስር የሚሰራ አንድ ልዩ ጽሕፈት ቤት ተቋቁሟል::

የዚህ ጽሕፈት ቤት ተግባሮች እንደሚከተለው ይሆናሉ:—

ሀ. ስለ ኢትዮጵያ አብዮት ሂደት በውጭ አገር ቋንቋዎች ጽሁፍ እያዘጋጀ ለተራማጅ ድርጅቶች ማሰራጨት፣

ለ. በቅርቡ ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ጋር በመተባበር በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔዎች ላይ በመመሥረት ጽሑፎችን በውጭ ቋንቋዎች ማሰራጨት፣

ሐ. የማህበራችንን የፖለቲካ መሥመር የማይጻረሩ ከሃገር ቤትም ሆነ ከሌሎች ስፍራዎች የሚገኙ ጠቃሚ ጽሑፎችን እየተረጐመ ማሰራጨት::

<u>ስለ አ/ኢ/ተ/ማ ህገ ማህበር</u>

እስከ አሁን ድረስ ማህበራችን ሲጠቀምበት የቆየው ህገ ማህበር በ1963 የወጣው በመሆኑ፣ይህ ህገ ማህበር በተለይም አሁን አገራችን ከሚ

ገንዘው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይዛመድ መሆኑን በመገንዘብ በተለይም ደግሞ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውና በቀርንጫፍ ማህበራት መሃል ያለው የሥራ ክፍፍልና የቀርንጫፍ ማህበራትን ተግባሮች የሚመለከቱት አንቀጾች ግልጽ ሆነው ባለመቀመጣቸው ይህን ሕገ ማህበር ለማሻሻል ከ7/8 እስከ14/8 የተሰበሰበው 17ኛው የኢ/ኢ/ተ/ማ ጠቅላላ ጉባዔ ሙሉ ስምምነት ላይ ከደረሰ በኋላ አንድ የተሻሻለ ህገ ማህበር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ለ18ኛው ጠቅላላ ጉ- ባዔ እንዲያቀርብ ያስባል::ለዚህም ቀርንጫፍ ማህበራት በቀድሚያ በፊ ውይይት እንዲያደርጉበት የህገ ማህበሩን ንድፍ ቀደም ብሉ እንዲያስራጭ ጉባዔው ያሳስባል::

በተጨማሪ ህገ ማህበሩ ተሻሽሉ በጠቅላላ ጉባዔ እስከሚጸድቅ ድረስ በቀርንጫፍ ማህበራትና በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው መሃከል የሚኖረዉ የሥራ ክፍፍልና የሥራ ዘዴ፣በህገ ማህበሩ ላይ ከተጠቀሰው ሌላ፣በሚቀጥለው እንዲሆን ጉባዔው ተስማምቶበታል::

ሀ. የጠቅላላ ጉባዔውን ውሳኔዎች ተከትሉ ጠቅላላ ማህበሩን የሚወክሉ ጸሐፎችን፣መምሪያዎችን፣መግለጫዎችን ማውጣት የሚችለው የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ይሆናል::

ለ. የማህበሩን ጠቅላላ አቋም የሚመለከቱ አዳዲስ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ወቅት ቀርንጫፍ ማህበራት አቋም ከመውሰዳቸው በፊት ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውን ማወያየት ይኖርባቸዋል::

ሐ. ውስጣዊ ማህበራት የማህበራችንን የማዕከላዊ ዲሞክራሲ የአሰራር ዘዴ በመከተል የሚያደርጉት ግንኙነት በቀርንጫፍ ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አማካኝነት መሆን ይኖርበታል::

<u>ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን ብሉ እራሱን ስለሚጠራው የግለገል ፋሺስቶች ቡድን</u>

አድሃሪያች የኢትዮጵያን አብዮት ከውስጥ በመቦርቦር፣ከውጭ በመከበብና ከዓለም የጭቁን ሕዝቦች ለማግለል ለሚያደርገው የተቀናበረ ዘመቻ የኢህአፓ የውጭ አካል የሆነው የግለገል ፋሽስቶች ቡድን እራሱን "ፌዴሬሽን ብሉ የሚጠራው፣የአብዮት ጠላትነት ሚናውን በሰፊዉ እያካሄደ ነው:: ይህ ቡድን፣በተለይም የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ትግል፣የትግሉ ዓላማ፣ያገኛቸውን ድሎች ወዘተ.. ለተራማጅ የዓለም ሕዝቦች እንዳይዳረስ፣የተገኙትንም ድሎች እንቋሽሽ ለማቀረብና ፀረ አብዮት ሃይሎችን ለመሰብሰብ ቆርጦ የተነሳ ነው::



"ፌዴሬሽን" በፖለቲካ ክስረት ከሰፊው ወጣት ተተፍቶ ከመውጣቱም አልፎ፣ደርጅቱታዊ ቀውስ ደርሶበታል::ከሶሺያሊስት አገሮች መሠረቱ እየተነቀለ ሲሄድ በሌሎች በታዎች ደግሞ ሙፈረካከስ አዝማሚያ ይዞአል::ለ" ኢህአፓ" ለ" ኢሊሰሌፍ"ና ለ"ኢዲዩ" የቀጥር ነፍስ ገዳዮች መመልመያ ገበያ ሆኗል:: ጋዜ ፍቀረ መርዕድን የገደሉ ሙሉጌታ ሉልሰጣንና ይትባረክ እስቂያስ በአሜሪካን ሰልጥነው የገቡ የኢዞና/ፌዴሬሽን ምልምሎች መሆናቸው ይህንን ሃቅ ያሳያል::በተጨማሪም "ፌዴሬሽን" ለቢሮይሌና ለአድሃሪው ቢሮክራሲ በሳይነት ማሰልጠኛ ድርጅት ከመሆኑም በላይ በቀጥታ ኢንፎርሜሽን አቀባይ ሆኗል::በህዳር ወር "ዝ ሁ ኢዝ ሁ" በሚል ርዕስ የወጣው የ30 ታጋዮች የስም ዝርዝርና የሕይወት ታሪክ በማውጣት ያደረገው የይፋ በለሳ ይህንኑ ያሳያል::

በለዚህ፣ ከ7/8እስከ14/8 በሉዛን ከተማ የተደረገው የኢ/ኢ/ተ/ማ 17ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የዚህን የፋሺስት ግለገል ቡድን በኢትዮጵያ ሕዝብ ጉን በመሰለፍ በተለይም በውጭ አገር ለሚያደርገው ፀረ አብዮት ሤራ በገንባር ቀደምነት ማህበራችን መታገል እንዳለበት ያረጋግጣል::

THE ETHIOPIAN STUDENTS' UNION IN EUROPE

## መ ዝ ሙ ር

### መልዕክት ይድረስ

መልዕክት ይድረስ ለታጋዮች
በየስፍራው ላሉት ጓደች
በርቱ በርቱ ታገሉለት
ለጭቁን ሕዝቦች ነፃነት

አ ዝ ማ ች

ታገል እስከመጨረሻው
ሕይወትህንም ሰዋለት
ገንባርህን ስጥ ተጋፈጠው
እስኪደመሰስ አድኃሪው

አ ዝ ማ ች

እስመሳዩ ይጋለጣል
አድርባዩ ይደመሰሳል
በደምህ ፍትህ ይገኛል
ጭቁን አርነት ይወጣል

አ ዝ ማ ች

አይረሳም የታጋይ ሞት
ለኩልነት ለነፃነት
በታጋይ ደም ታበባለች
የጭቁን ሕዝቦች ነፃነት

አ ዝ ማ ች

ገና ብዙ ይሞታሉ
ሌሎች ጓዶች ይተኪሉ
በጭቁኖች የትግል ፋና
እስከገነበታ ለዱሉ፡፡

አ ዝ ማ ች

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፣

የውጭን ንቅናቄ ከውስጥ ሆኖ ቦርቦሮ ለማዳከም ያደረገው ሙከራ ስላልተሳካለት እርሱን ከንቅናቄያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ያለማቋረጥና ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግሉ ሲያካሂድ በኖረው ማህበራችንና በነዚሁም አስር ዓመታት ያስተጠማቸውን ነፃነት በመንጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፣ከየተናጠሙ የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መተንፈሻ ሆነው በቆዩት በታጠቅና በትግላችን ስም መጠቀም ጀምረዋል፡፡ የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም ታጠቅና ትግላችን በአስር ዓመት ቆራጥ ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖሊሲውን ለመሸፈን ነው፡፡እንዲሁም ከውጭ ሆኖ ያቋቋሙን የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ወሽንገበር በመገዛት ለማፋፋም ነው፡፡ይህም እንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው፡፡ ለማገናዘብ፣የተለመደው የመጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያልያዙ፣ የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አባልነትን የማያመለክት ግን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንድትታወቁልንና እንዲታስታውቁልን እንጠይቃለን፡፡ለእነዚሁ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው "ዓለም ዓቀፍ ፊዴሬሽን" በሚባል ስም የታወቀው የነ አስፋወሰን — መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው፡፡

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአኢተማ የመጽሄት አዘጋጅ ቦርድ